# የመምህሩ መምሪያ

## የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ደረጃ 3 እና 4

## ተከታታይ ትምህርቶች 1-6

www.besweb.com

# የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት

በሕግ የተመዘገበ የዩናይትድ ኪንግደም ለጋሽ ድርጅት (የምዝገባ ቁጥር 1096157)

**ተልእኮ**

በአለም ዙሪያ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ እንዲሁም በዚህ ዘመን ያለውንና የወደፊቱን ትውልድ የእግዚብሔርን ቃል ለማስተማር የሚረዱ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በማዘጋጀት ሰዎችን ማገልገልና ለአገልግሎት ብቁ ማድረግ።

***ራዕይ***

የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አይነቶችን ስራ ላይ በማዋልና ዋና ዋና እሴቶቻችን ከሚጋሩ ግለሰቦች ጋር አብሮ በመስራት በተለየዩ የዓለም ቋንቋዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ዝግጅትን ማበረታታት።

## አጠቃላይ መረጃ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባራት ምንድናቸው?**

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት "ዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ"፣ "አዲስ ሕይወት" እና "ቃራሚዎች" በሚል ርዕስ የሚታወቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በእንግሊዝኛ ያሳትማል። እንዲሁም በምድረ እንግሊዝና በሌሎች የዓለም ክፍሎች በፖስታ ቤቶች አማካኝነት በመላላክ እነኝህን ትምህርቶች የሚሰጡ የርቀት ትምህርት ቤቶችንና ሌሎች ድርጅቶችን በጉብኝት፣ በምክር፣ በኔትወርኪንግና በስልጠና ያግዛል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ በትርጉም፣ በዲዛይን፣ በሕትመትና ትምህርቶችን በማሰራጨት ከሚሰሩና በሌሎች አገሮች ውስጥ ከሚገኙ ቡድኖች ጋር አብሮ ይሰራል። ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርቶቹ በነፃ እንዲዳረሱ ማድረግም ሌላው የመጽሐፍ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባር ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቶች በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉት በደቡብ አየርላንድ ከ50 ዓመታት በፊት ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በእንግሊዝኛና በሌሎች የውጭ አገር ቋንቋዎች የሚዘጋጁ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን የኤዲቶሪያል ኃላፊነት ይወስዳል። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሕትመት በኤ 4 ፎርማት ሆኖ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች በአራት ሳምንት አንድ ጊዜ ትምህርቶችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማዕከል ለእርማት መላክ እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለቤት ለቤት ጀማ ወንጌል (የተሐድሶ ንቅናቄ) ምስጋና ይግባውና በቤልፋስት የ6 ወራት ትምህርቶች በኤ 5 ፎርማት ማዘጋጀት ተችሏል። ይህም ትምህርቶች በት/ቤቶችና በየአብያተ ክርስቲያናቱ በቀላሉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስችሏል። ይህ ደግሞ ጥሩ የፖስታ አገልግሎት በሌለባቸው አካባቢዎች ውጤታማ ሆኗል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ኮርሶችን ልዩ የሚያደርጋቸው የቤት ለቤት ወይንም ደግሞ በቤተ ክርስቲያንና በት/ቤቶች የሚካሄዱ የቡድን ጥናቶችን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተውና በሚገባ የታቀደ ሲለበስን ተከትለው ተማሪዎች ጥናታቸውን እድሜያቸው 20 ዓመት እስኪሆነው ድረስ እንዲቀጥሉ ስለ ሚረዷቸው ነው። ለየእድሜ ደረጃው የሚመጥኑ በአምስት ደረጃዎች የተከፋፈሉ ትምህርቶች ቀርበዋል። ቅድመ መደበኛ ትምህርት፣ ከ5-7 ዓመት፣ ከ8-10 ዓመት፣ ከ11-13 ዓመት፣ ከ14-16 ዓመት። ለእያንዳንዱ የእድሜ ክልል የሶስት ዓመት ሲለበስ ተዘጋጅቷል። (ገፅ አራትን ይመልከቱ።) እያንዳንዱ የእድሜ ክልል ባሉት ችሎታዎች መሠረት ይለያያል። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያጠኑ እድል ይፈጥርላቸዋል። ይህም የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እንዲማሩና ወንጌልን በሕይወታቸው ለመተግበር በሚያደርጉት ጥረት የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች መጋፈጥ እንዲችሉ በማገዝ ነው።

የእነኝህ ትምህርቶች ኮፒዎች በእንግሊዝኛ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት **(www.besweb.com)** ላይ ማውረድ ይቻላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አብረውት በአጋርነት መስራት ለሚፈልጉ ሰዎች የሚጠቅሙ ዶክሜንቶች አሉት። እነኝህ ዶክሜንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት ላይ ይገኛሉ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አድራሻዎች


**ዓለም አቀፍና የሰሜን አየርላንድ ፀሐፊ (የሁሉም ትምህርቶች አከፋፋይ)**
Mr S Balmer, 37a Belmore Street, Enniskillen, Northern Ireland BT74 6AA
ስልክ: 0286 632 2462
ኢሜይል: sam@besweb.com

**የዩናይትድ ኪንግደም ፀሐፊ**
Mr Stephen Gillham, 32 Firs Glen Road, West Moors, Ferndown, Dorset BH22 0ED
ስልክ: 01202 873500
ኢሜይል: stephen@sgilllham.co.uk

**ዌብ ሳይት**: www.besweb.com
**የኢሜይል አድራሻ**: info@besweb.com

## *ለመምህራን መምሪያዎች*

የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች በመጀመሪያ ሲዘጋጁ በፖስታ በመላላክ ለማስተማር ታስበው ነበር። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የፖስታ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ማዕከላት ተቋቁመው ነበር። ነገር ግን የፖስታ አገልግሎት አስተማማኝ ባልሆነባቸው እስከጭራሹንም እየቀረ በሚሄድባቸው ስፍራዎች በተለይም ደግሞ በአፍሪካና በሕንድ እንዲሁም በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለሚጠቀሙ የማስተማሪያ መምሪያዎችም ተዘጋጅተዋል። በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተዘጋጁት የመምህሩ መምሪያዎች ታሳቢ ያደረጉት ደረጃ 3 እና 4ን በግምት እድሜያቸው ከ11-14+ ዓመት የሆኑ ልጆችን ነው።

እያንዳንዱ የመምህሩ መምሪያ ልክ *በዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ* ትምህርት ውስጥ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና መምሪያዎቻቸው በየሳምንቱ እንዲጠኑ ተደርገው ተዘጋጅተዋል። የሚያዚያ ትምህርቶች በተለይ ከፋሲካ ጋር የተገናኙ ትምህርቶች ሲሆኑ የታህሳስ ትምህርቶች ደግሞ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር የተገናኙ ናቸው።

በአንዳንድ ቦታዎች በኤ 4 የወረቀት መጠን የሚዘጋጀውን ሳምንታዊ ሕትመት ሲጠቀሙ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ 24 ትምህርቶችን የያዘውንና በኤ 5 የወረቀት መጠን የተዘጋጀውን ጥራዝ ይጠቀማሉ። መምህሩ ወይንም ደግሞ የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ በኤ 4 የወረቀት መጠን ትምህርት ያድላል። ትምህርቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይንም ደግሞ በት/ቤት ይሞላል ወይንም ደግሞ ወደ ቤት ይወሰዳል። ከዚያም በተከታዩ ሳምንት ይመለሳል። በወሩ መጨረሻ መምህሩ ወይንም የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ ትምህርቶችን ይሰበስብና ያርማቸዋል። ነጥብም ይሰጣቸዋል። በተቻለ መጠንም ከእርማት በኋላ ለተማሪዎች መመለስ አለበት።

የተዘጋጁት ጥራዞች ጥቅም ላይ ከዋሉ በየሳምንቱ መጨረሻ እየተሰበሰቡ ይታረማሉ። በብዙ ምክንያቶች ይህ አስቸጋሪ እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህም በክፍል ውስጥ ጥራዞቹ ለተማሪዎች ይከፋፈላሉ። በዚህ ጊዜ መምህሩ/መሪው ከተማሪዎች ጋር አብሮ ይሰራል። ተማሪዎችም የጓደኞቻቸውን ስራዎች ያርማሉ፣ ነጥብም ይሰጣሉ። ከጥራዞቹ በስተጀርባ ለእያንዳንዱ ነጥብ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ እንዲሁም ተማሪው ስላሳየው እድገት አስተያየት መስጫ ቦታ አለ። እንዲሁም ከጥራዙ በስተመጨረሻ ሰርተፊኬት ተያይዟል። ይህ ሰርተፊኬት በቀላሉ ከጥራዙ ላይ ሊገነጠል የሚችል ሲሆን ተማሪው ባለፉት 6 ወራት ከመቶ ያገኛቸውን ውጤቶች ይይዛል።

## *ለመምህራን የተደረገ ዝግጅት*

*መምህራን በራሳቸው ዘዴ ወይንም መንገድ፣ ተነሳሽነትና ሀሳብ ላይ የተመሠረተ አንዳችም ነገር እንዲያደርጉ አንጠብቅም። ለእንደዚህ አይነት ጉዳይ ምንም ቦታ አንሰጥም። የሚከተሉት ሀሳቦች የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ሀሳቦች ናቸው።*

- **ከታሪኩ ጋር በሚገባ ራስን ማስተዋወቅ** - ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና በተጓዳኝ አብረውት ከሚሄዱት የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር በተቻለ መጠን ራሳቸውን ማስተዋወቅ አለባቸው። መምህሩ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከማስተማሩ በፊት ራሱ አጥንቶ ቢያጠናቅቅ ተመራጭ ነው። ለእያንዳንዱ ትምህርት የተዘጋጁት መምሪያዎችም በእቅድ ወቅት ስለ ሚረዱ በጥንቃቄ ሊታዩ ይገባል።
- ***ትምህርቶችን በሚገባ መረዳት*** - ከእያንዳንዱ የትምህርት እቅድ በላይ *"በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።"* የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። እነኝህም መምህሩ ገለፃውን ካጠናቀቀ በኋላና ተማሪዎችም ያንን የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የሚጨብጧቸውን ሁለት አላማዎች የያዙ ናቸው። የመጀመሪያው አላማ ከታሪኩ ስለ ቀሰሙት እውቀት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ስላገኙት እውቀት እንዲያሰላስሉና በተቻለ መጠንም ምላሽ እንዲሰጡና ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት ያበረታታል። እነኝህ የመማር አላማዎች በተሰጠው ትምህርት ውስጥ ያለውን ዋና ፅነሰ ሀሳብ/እውነት የያዙ ናቸው። መምህራንም ራሳቸውን እንዲሁም የመማር የማስተማር ሂደቱን ለመገምገም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።
- ***አስተዋውቁት/መግቢያ*** - *ሁሉንም ትምህርቶች የምንጀምረው ከራሳቸው ከተማሪዎች ልምምድና ካሉበት ሁኔታ በመነሳት ነው። ታሪኮችን በመግቢያው ውስጥ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ዘዴዎችን አቅርበናል። በዚህም ልጆች በትምህርቱ ማስጀመሪያ ነጥብ ላይ በመስተጋብር የተሞላ ውይይት እንዲያካሂዱ እናስችላቸዋለን።*
- **የማስተማር ጊዜ** - *የታሪኩን ቁልፍ ነጥቦች አቅርበናል። መምህራን ታሪኮቹን በሚያስተምሩበት ወቅት እነኝህን ቁልፍ ነጥቦች እንደማያነሷቸው ተስፋ እናደርጋለን። ሆኖም በሚያስምሩበት ወቅት ራሳቸውን ከታሪኩ ጋር በሚገባ አስተዋውቀው ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተማር ይጠቀሙባቸዋል። መምህሩ በትምህርቱ ውስጥ ያለውን ታሪክ ተማሪዎቹ በሚገባ እንዲረዱ ማድረግ አለበት። እንዲሁም ልጆቹ ታሪኩን ከተገነዘቡት በኋላ መስጠት ስላለባቸው ምላሽ አቅጣጫ ይጠቁማቸዋል። ከእያንዳንዱ ትረካ ጋር አብሮ የሚሄዱ ማብራሪያዎችንም አብረን ማቅረቡ ተገቢ ስለሆነ ይህንኑ አድርገናል። እነኝህም በኢታሊክስ (ITALICS) ተፅፈው ቀርበዋል።*
- **የመማር ጊዜ** - *ከእያንዳንዱ ታሪክ ጋር አብሮ የተያያዘ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለ። አንዳንድ ጊዜም ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተያይዘዋል። ምክንያቱም ተጨማሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተማሪዎች በቀላሉ መማር እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ልጆች እነኝህን ቁልፍ ጥቅሶች እንዲማሩ እንዲሁም በተደጋጋሚ እንዲያስታውሱት እንደሚደረግ ተስፋ እናደርጋለን። ይህም ልጆች የቁልፍ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እውቀት ግንባታ ማድረግ እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል።*
- **ማጠናቀቅ** - *በት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች ሰርቶ ማሳያ/የመለማመጃ ጥያቄዎችን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋቸውን የችሎታ ልክና መምህሩ በዚህ ረገድ ለተማሪዎቹ ሊያደርግላቸው የሚችለውን የእገዛ መጠን በተመለከተ ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል። አንዳንዶች መምህሩ ታሪኩን ካነበበላቸውና ከታሪኩ ጋር በሚገባ ከተዋወቁ በኋላ ወደ ስራ ይገባሉ። ሌሎች ልጆች ደግሞ ታሪኩን ራሳቸው ማንበብ ይችላሉ። በሁለቱም መንገዶች ዋናው ሀሳብ ጥያቄዎቹን ለመስራት በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የልጆቹ አትኩሮት እንዲያርፍ ማድረግ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከት/ቤት ውጪ በሌሎች ቦታዎች የምትጠቀሙ ከሆነ ተማሪዎቻችሁን ባሉበት ቦታ በአካል ተገኝታችሁ መርዳት መቻል አለባችሁ። አለበለዚያ ተማሪዎቻችሁ ትምህርቱን እንደፈተና ወይንም ደግሞ የግድ መጠናቀቅ እንደላበት ስራ አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ። አስደሳች መሆን አለበት። ለዚህም ተማሪዎች እየሰሩ ባለበት ወቅት ማበረታታት አስፈላጊ ነው።*
- **የክለሳ ጊዜ** - *በተቻለ መጠን ተማሪዎች በምን ያህል መጠን ትምህርቱን አውቀውታል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዱንን አጫጭር ሙከራዎችን መስጠት ወይንም አስፈላጊ መሆኑን እንመክራለን። ይህም ትምህርቱን ለመከለስና የተማሪዎችን የመማር ፍጥነት ለማገዝ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።*
- **ማሳየት** - *በአንዳንድ ሁኔታዎች የቪዡዋል (የእይታ) ትምህርት መርጃዎች በቀላሉ ላይገኙ ቢችሉም በተቻለ መጠን ለሚታዩ ስዕሎች ወይንም ደግሞ ለሌሎች ቁሳቁሶች ትኩረት መስጠትና በተግባር ማዋል ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል።*

በትረካ ወቅት የእይታ ትምህርት መርጃዎች ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ። አስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችን በተመለከተ መረጃ ከተፈለገ ከሚከተለው ዌብ ሳይት ማግኘትና ስዕሎችንም ማውረድ ይቻላል። [www.freebibleimages.org (FBI)] ሌላው የእይታ መርጃዎችን የምናገኝበት ምንጭም Eikon Bible Art [info@eikonbibleart.com] ዌብ ሳይት ነው። ሆኖም ከዚህ ዌብ ሳይት የምናገኛቸው ምንጮች በሽያጭ የሚገኙ ናቸው። የፎቶ ኮፒ ማሽን ባለበት አንዳንድ ስእሎች ሊተልቁ ቀለም ሊቀቡና በትምህርት ወቅት ጥቅም ላይ ማዋል ሊውሉ ይችላሉ።

**ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የማስተማር ጊዜ**

1) ጥቅሱ በወረቀት ወይንም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሊፃፍ ይችላል። ይህም የተለያዩ ቃላትን በማጉደል የሚደረግ ነው። ይህም ሁሉም የጥቅሱ ቃላት በሙሉ እስኪነሱና ተማሪዎችም ጥቅሱን በቃላቸው መድገም እስኪችሉ ድረስ ነው።
2) ቁልፍ ጥቅሱን ለማስተዋወቅ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ።
   ሀ) በሁለት ቡድኖች መስራት (በገመድ የመስቀል ዘዴ) – የቁልፍ ጥቅሱ የተለያዩ ፊደላት ተቀንሰው በምትካቸው ክፍት ቦታዎች አሉ። ልጆችም የትኞቹን ቃላት ቢጠቀሙ ጥቅሱን ማሟላት እስከሚችሉ ድረስ ይሰራሉ። ይህም ከመካከላቸው አንደኛው ልጅ ጥቅሱን እስከሚለየው ድረስ ይቀጥላል።
   ለ) ጥቅሱን ቀድሞ መፈለግ። መጽሐፍ ቅዱስ በቀላሉ የሚገኝ ከሆነ ተማሪዎች ቁልፍ ጥቅሱን ይፈልጋሉ። መጀመሪያ ጥቅሱን ያገኘው ልጅ አሸናፊ ይሆናል።

**ጊዜን ማቀድ**

- **ቅደም ተከተል** ለሁሉም የማስተማሪያ መምሪያዎች ተመሳሳይ ቅደም ተከተል እንጠቀማለን። ሆኖም ይህን ቅደም ተከተል መምህራን እንደአስፈላጊነቱ ሊቀያይሩት ይችላሉ።
  - o መግቢያና ትረካ - በግምት 15 ደቂቃ
  - o ቁልፍ ጥቅሱን የማስተማር ጊዜ – ከ5 እስከ10 ደቂቃ
  - o ስርቶ ማሳያውን ማጠናቀቅ - 20 ደቂቃ
  - o መልመጃና ሌሎች ስራዎች 5-10 ደቂቃ

ይህን አባባል ሁሌም አስታውሱት።

“የነገራችሁኝን እረሳለሁ።
የምታሳዩኝን አስታውሳለሁ።
አብሬያችሁ ስሰራ በሚገባ እረዳለሁ።”

## የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሲለበስ

| | ደረጃ 0 (ቅድመ መደበኛ ትምህርት)<br>ደረጃ 1 (ከ5-7 ዓመት)<br>ደረጃ 2 (ከ8-10 ዓመት) | ደረጃ 3 (ከ11-13 ዓመት) | ደረጃ 4 (14 ዓመትና ከዚያ በላይ) |
|---|---|---|---|
| የጀማሪዎች ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል |
| ሀ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. ፀሎት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረትና ውድቀት<br>2. ዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ክንዋኔዎች<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. የክርስቲያን ሕይወት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ለ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የክርስቶስ የቀደመው ሕይወቱ<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. ምሳሌዎች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሰስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ፀሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሰስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ያዕቆብና ቤተሰቡ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የሐዋርያት ስራ 2፡42 ከፊት ለፊት ያለው መንገድ<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሕግ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ሐ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ዳንኤል<br>2. ተጨማሪ ተአምራት<br>3. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሳሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ዮናስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>3. ተጨማሪ ተአምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. እግዚአብሔር የተጠቀማባቸው የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. የኢየሱስ አባባሎች<br>3. የጌታ ኃይል<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ተጨማሪ የብሉይ ኪዳን ባሕርያት<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |

| | ሀ1 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – በመጀመሪያ<br>ርዕስ – እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ። | ሀ1 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – ፍጥረት<br>ርዕስ – በመጀመሪያ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *ዘፍጥረት 1: 1-19*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ**: *ዘፍጥረት 1: 1*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br><br>1. እግዚአብሔር አለምንና በውስጧ ያለውን ሁሉ ፈጠረ።<br>2. እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ፈጠረ። የፈጠረውን እያንዳንዱንም ሰው ያውቃል ደግሞም ይወዳል።. | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *ዘፍጥረት 1: 1-31*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ**: *ዕብራውያን 1: 10፤ ኢሳያስ 45: 18*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br><br>1. እግዚአብሔር አለምን ፈጠረ። uniቁጥር.<br>2. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።<br>3. እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ። |
| *መግቢያ* | እያንዳንዱ ተማሪ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ አድርጉ። መላምት መጠቀምም ጥሩ ነው። ከዚያም መልሶቻቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር መጋራት ይችላሉ።<br><br>1. በሕዋው ውስጥ ስንት ከዋክብት ይገኛሉ?<br>2. በዓለም ውስጥ ስንት ሰዎች ይገኛሉ?<br><br>ከደቂቃዎች ቆይታ በኋላ የሚከተሉትን መልሶች አሳዩ።<br>• እንአውሮፓ የሕዋ ኤጀንሲ በሕዋ ውስጥ ምን ያህል ከዋክብት እንዳሉ መናገር ይከብዳል። በግምት ወደ አንድ መቶ ሺ ሚሊዮን ከዋክብት እኛ ባለንበት ጋላክሲ በሚልኪ ዌይ ውስጥ ብቻ እንደሚኖሩ ይታመናል። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ጋላክሲዎች በሕዋ ውስጥ ይገኛሉ። ያ ማለት ደግሞ ስፍር ቁጥር የሌላቸው እጅግ ብዙ ከዋክብት በሕዋ ውስጥ<br>• በአሁኑ ጊዜ በአለም ውስጥ ወደ ሰባት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች እንዳሉ ይገመታል። | የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጀመሪያ በጥንድ ተወያዩባቸው። ከዚያም ክፍሉ በሞላ በአንድ ላይ ይወያይባቸው።<br><br>የፈጠራ ችሎታችሁን ተጠቅማችሁ አንድ ነገር የሰራችሁት መቼ እንደሆነ መናገር ትችላላችሁ?<br><br>ባያችሁት ውጤት ደስተኞች ናችሁ? |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>1. ከምንም ነገር በፊት እግዚአብሔር ነበር።<br>2. እግዚአብሔር አለምን በስድስት ቀናት ፈጥሮ አጠናቀቀ።<br>3. በመጀመሪያው ቀን እግዚብሔር ብርሃንን ፈጠረ። ከጨለማም ለየው። በሁለተኛው ቀን እግዚአብሔር ሰማይን ፈጠረ። በታች ካለው ውኃም ለየው። በሶስተኛው ቀን እግዚአብሔር ውኖችን በአንድ ላይ ሰበሰባቸው። ደረቁንም የብስ ምድር ብሎ ጠራው። ምድር አትክልቶችንና ዛፎችን አስገኘች። በአራተኛው ቀን እግዚአብሔር በሰማይ ብርሃናትን አኖረ። እነኝህም ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ናቸው። በአምስተኛው ቀን እግዚአብሔር የባሕር እንስሳትንና አእዋፍን ፈጠረ። በስድስተኛው ቀን ደግሞ ሌሎች እንስሳትን ፈጠረ።<br>4. ከዚያም እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ። ወንድና ሴትም አድርጎ ፈጠራቸው። ምድርንም እንዲሞሉና ምድርንና በውስጧ ያሉትን ፍጥረቶች በሙሉ እንዲገዙ አደረጋቸው።<br>5. እግዚአብሔር ለፈጠረው ሰውና ለሌሎች ፍጥረታት በሙሉ የሚበሉት ምግብ አዘጋጀላቸው።<br>6. እግዚአብሔር የሰራውን ነገር ሁሉ ተመልክቶ መልካም እንደሆነ አየ።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ.** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>1. እግዚአብሔር አለማትን በስድስት ቀናት ፈጥሮ አጠናቀቀ።<br>2.***አንደኛ ቀን*** ፡ እግዚአብሔር ብርሃንን ፈጠረ ከጨለማም ለየው። ***ሁለተኛ ቀን:*** እግዚአብሔር ሰማይን ሰራ ከበታች ካለው ውኃም ለየው። ***ሶስተኛ ቀን:*** እግዚአብሔር ውኖችን በአንድ ላይ ሰበሰባቸው። ደረቁንም የብስ ምድር ብሎ ጠራው። ምድር አትክልቶችንና ዛፎችን አስገኘች። ***አራተኛ ቀን***: እግዚአብሔር በሰማይ ብርሃናትን አኖረ። እነኝህም ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ናቸው። ***አምስተኛ ቀን*** ፡ እግዚአብሔር የባሕር እንስሳትንና አእዋፍን ፈጠረ። ***ስደስተኛ ቀን:*** እግዚአብሔር ሌሎች እንስሳትን ፈጠረ።<br>3. የእግዚአብሔር ኃይል አስደናቂ ነበር። አለምን የፈጠረው ቃል በመናገር ብቻ ነበር። ይህን ለማድረግም ስድስት ቀናት ብቻ ፈጀበት።<br>4. እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው። ወንድና ሴትም አድርጎ ሰራቸው።<br>5. እግዚአብሔር የሰራውን ነገር ሁሉ ተመልክቶ መልካም እንደሆነ አየ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በአራት ቡድኖች ክፍሉን ከከፈላችሁ በኋላ እግዚአብሔር በየአንዳንዱ ቀን የፈጠራቸውን ፍጥረታት ፖስተር አዘጋጁ። | በዚህ ትምህርት ስለእግዚአብሔር ባሕርይ ምን ትምህርት አገኛችሁ? ይህን ማንፀባረቅ የሚችል አንድ ግጥም ጻፉ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው። ሁሉንም ነገር የፈጠረው እርሱ ነው። ምንም እንኳን ፍጥረቱ በጣም ትልቅና ብዙ ቢሆንም እግዚአብሔር ፈጥሮታል፤ እያንዳንዱን ፍጥረቱን ያውቃል፤ እያንዳንዳችንንም ይወደናል። ይህ ለእግዚአብሔርና ለፍጥረቱ ምን አይነት አመለካከት እንዲኖረኝ ያደርጋል? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>1. እግዚአብሔር አለማችንን ፈጠረ። ከዚያም እኛን ፈጠረ። ይህ በሕይወታችን ምን ለውጥ መፍጠር አለበት?<br>2. ***ዘፍጥረት 1: 26-27*** እና ***ኢሳያስ 45: 18ን አንብቡ።*** እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ምን ራዕይ ነበረው? ዛሬ ይህ እውነት በሕይወታችን ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ ይፈጥርበታል? |

| | ሀ1 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 –በመጀመሪያ<br>ርዕስ – እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ። | ሀ1 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 - ፍጥረት<br>ርዕስ – ተጠናቀቀ። |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: ***ዘፍጥረት 1: 20-31***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት 1: 27***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. እግዚአብሔር እንስሳትን ፈጠረ። ሰውን ግን ልዩ አድርጎ ፈጠረው።<br>2. እግዚአብሔር ልክ እንደእርሱ እንዲሆንና ፍጥረቱን እንዲገዛ ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ።<br>3. እግዚአብሔር ሰዎችን የፈጠረው ከእርሱ ጋር እንዲሁም እርስ በርሳቸው ግንኙነት እንዲኖራቸው አስቦ ነበው።<br>4. እግዚአብሔር እግዚአብሔር ለሰው ኃላፊነትን ሰጠው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: ***ዘፍጥረት 1: 27-31; 2: 1-9***<br>**ቁልፍ ጥቅስ :** ***የሐንስ 1: 1-3***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. እግዚአብሔር ሰባተኛው ቀን አረፈ።<br>2. እግዚአብሔር ሰንበትን ለእረፍት ፈጠረ።<br>3. እግዚአብሔር ለሰው ሕይወትን ሰጠው።<br>4. የሰው ሕይወት ልዩና ከፍተኛ ዋጋ አለው። |
| *መግቢያ* | ክፍሉን በአራት ቡድኖች ከፍሉትነ። ለእያንዳንዱ ቡድን ወረቀትና እስክርቢቶ ወይንም ደግሞ ማርከር አቅርቡለት። ከየቡድኑ አንድ ሰው የእንስሳት ስዕል ይስላል። ሌሎች የቡድኑ አባላት ደግሞ እንስሳው ምን እንደሆነ ይገምታሉ። | በመመላለስ የሚደረግ ክርክር። የሚከተሉት ፅሑፎች ያሉባቸውን ሶስት ጣቢያዎች በክፍል ውስጥ አዘጋጁ።<br>***"እስማማለሁ"፣ "አልስማማም"፣ "እርግጠኛ አይደለሁም"***<br>የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ለተማሪዎቻችሁ ታነቡላቸዋላችሁ። ተማሪዎችን የእነርሱን አመለካከት ወደ ሚያንፀባርቀው ጣቢያ ይንቀሳቀሳሉ።<br>• እሁድ ልዩ ቀን ነው የሚለው ሀሳብ በአሁኑ ዘመን ተቀባይነት የለውም።<br>• እሁድ የቤት ስራ ለመስራትና ለመገበያየት ትክክለኛው ቀን ነው።<br>• በእሁድ ቀን ስፖርት መስራት የተከለከለ ነው።<br>• በፅንስ ላይ የሚካሄድ የሜዲካል ምርምር ተቀባይነት የለውም።<br>• ክርስቲያኖች በጦርነት መሳተፍ የለባቸውም። |
| *ማጠናቀቅ* | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>***ውይይትና ገለጻ***<br>1. እግዚአብሔር እንስሳት እንዲዋለዱና እንዲባዙ ፈጠራቸው።<br>2. እግዚአብሔር ሰዎች እንደእርሱ እንዲሆኑ፣ በአሶች፣ በወፎችና በእንስሳት ላይ የበላይ እንዲሆኑ አድርጎ በራሱ አምሳል ፈጠራቸው።<br>3. እግዚአብሔር ሰዎችን ፈጠረ። ወንዶችና ሴቶች አድርጎ ሰራቸው።<br>4. እግዚአብሔር ለሰዎች የተለየ ስራን/ኃላፊነትን ለሰዎች በመስጠት ባረካቸው። ባረካቸው። (እንዲዋለዱና እንዲባዙ፣ ምድርን እንዲሞሏትና እንዲገዟት፣ እግዚአብሔር በፈጠራቸው ፍጥረታት ላይ የበላይ እንዲሆኑ።)<br>5. እግዚአብሔር ሰዎችን ጨምሮ ለሁሉም ፍጥረታት የምግብ ምንጮችን አዘጋጀ።<br>6. እግዚአብሔር በሰራው ነገር ሁሉ ደስ ተሰኘ። ሁሉም መልካም ነው አለ!<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። *ተማሪዎችም እንዲያጠኑት* አበረታቷቸው።**<br>**ትም*ህርት ሁለትን* አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>***ውይይትና ገለጻ***<br>1. እግዚአብሔር ምንም ነገር ከመፈጠሩ በፊት ነበር። ቃሉ (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ) አግዚአብሔር ነበር። ከእግዚአብሔር ጋርም ነበር። የተፈጠረውን ነገር ሁሉ ፈጠረ። ያለእርሱ የተፈጠረ ምንም ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው። የጅማሬዎች ሁሉ አምላከ ነው።<br>2. እግዚአብሔር ሰውን በኤደን ገነት አኖረው።<br>3. እግዚአብሔር ሁለት ልዩ ዛፎችን በኤደን ገነት አስቀመጠ። እነርሱም የሕይወት ዛፍና መልካሙንና ክፉውን የምታስታውቀው ዛፍ ናቸው።<br>4. እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን አረፈ። ሰውም በዚህ ልዩ ቀን እንዲያርፍ ደነገገ።<br>5. እግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስን በሰው ላይ እፍ አለበት። ይህ ሰውን ከሌሎች እንስሳት ልዩ አደረገው። የሰው ሕይወት ልዩ ነው። ዋጋው ትልቅ ነው።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። *ተማሪዎችም እንዲያጠኑት* አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት *ሁለትን* አጠናቁ። .** |
| ክለሳ | በትንንሽ ቡድኖች ሆናችሁ ተወያዩ። ከዚያም ለክፍሉ በሞላ ግብረ መልስ ስጡ። እግዚአብሔር ሰዎች በአሶች፣ በወፎችና በእንስሳት ላይ የበላይ እንዲሆኑ አድርጎ በራሱ አምሳል ፈጠራቸው። እንዴት ነው ልንከባከባቸው የሚገባን?<br><br>እግዚአብሔር ከእርሱና ከሌሎች ጋር ግንኙነት እንዲኖረን አድርጎ ፈጠረን። ለእግዚአብሔርና ሌሎች ሰዎች ያለንን ፍቅር የምንገልፀው እንዴት ነው? 1)በቤት 2) በት/ቤት 3) በቤተ ክርስቲያን ? | በትንንሽ ቡድኖች ሆናችሁ ተወያዩ። ከዚያም ለክፍሉ በሞላ ግብረ መልስ ስጡ።<br>***ዘፀአት 20: 8*** እና ***ማርቆስ 2: 27*** አንብቡ። እነኝህ ጥቅሶች ዛሬ ለእኛ አስፈላጊነታቸው ምንድነው?<br><br>የሰው ሕይወት ልዩ ዋጋ እንዳለው ተምረናል። ይህ እውነት በሳይንሳዊ፣ በሜዲካል፣ በሕጋዊ ውሳኔዎች ላይ ያለው ተፅእኖ ምንድነው? የዕድሜ ባላጠጎችን በመርዳት ረገድ ያለው ወሳኝነት ምንድነው? |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | ***ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?***<br>1. እግዚአብሔር ከእርሱና ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት እንዲኖረን አድርጎ ፈጠረን። እግዚአብሔርን በየቀኑ ብንታመንበትና ብንናዘዝ በሕይወታችን ምን ለውጥ ያመጣል?<br>2. እግዚአብሔር በዚህ ሳምንት በቤተሰባችን፣ በት/ቤታችን እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኃላፊነታችንን እንድንወጣና ከእርሱ ባሕርያት የተወሰኑትን በየእለቱ ማንፀባረቅ እንድንችል እንዲረዳን መፀለይ አለብን። (ለምሳሌ ያህል ፍቅሩን፣ ርህራሄውን፣ ቅን ፈራጅነቱን) | ***ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?***<br>1. የሰንበት እረፍትን ተሳክቶልን ማሳለፍ የምንችለው እንዴት ነው? የሰንበት እረፍት አስፈላጊ ነው? ለምን?<br>2. የሰው ሕይወት ከእግዚአብሔር የተሰጠና ልዩ ዋጋ እንዳለው በሕይወታችን የምናረጋግጠው እንዴት ነው? |

| | ሀ1 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 - በመጀመሪያ<br>ርዕስ – ነገሮች መበላሸት ጀመሩ። | ሀ1 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 - ፍጥረት<br>ርዕስ – የኃጢአት መጀመር |
|---|---|---|
| | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: *ዘፍጥረት 2: 15-17; ዘፍጥረት 3: 1-13*<br>ቁልፍ ጥቅስ: *ዘፍጥረት 3: 3*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. አዳምና ሔዋን የእግዚብሔርን ትዕዛዝ ተላለፉ።<br>2. አዳምና ሔዋን በሐፍረት ተሞሉ። የኃጢአታቸውን ዋጋም ይቀበላሉ። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: *ዘፍጥረት 2: 14-19; ዘፍጥረት 3: 1-7*<br>ቁልፍ ጥቅስ : *ሮሜ 3: 23; ሮሜ 6: 23*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. እግዚአብሔር ሰውን መልካምና ክፉን ከምታስታውቀው ዛፍ እንዳይበላ አዘዘው።<br>2. እባብ ሔዋንና አዳም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዲተላለፉ አሳታቸው።<br>3. አዳምና ሔዋን በድርጊታቸው አፈሩ። |
| መግቢያ | ተማሪዎች በሚማሩባቸው ት/ቤቶች ሕጎች እንዳሏቸው ጠይቋቸው። እነኝህ ሕጎች ለምን ያስፈልጋሉ? ሰዎች ችላ ቢሏቸው ምን ይከሰታል? | የሚከተሉትን በጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ተማሪዎቻችሁን ጠይቋቸው።<br>• በቤት/በስራ ቦታ/በትምህርት ቤት ስላላቸው ኃላፊነት።<br>• ሊከተሏቸው ስለሚገቡ ደንቦችና መመሪያዎች።<br>• እነኝህ ደንቦችና መመሪያዎች ችላ ቢባሉ ምን ይከሰታል? |
| ማጠናቀቅ | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br>ውይይትና ገለጻ<br><br>1. እግዚአብሔር ሰውን በኤደን ገነት አስቀምጦ እንዲንከባከባት አዘዘው። እግዚአብሔር ለሰው የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጠው። ነገር ግን ሰው ሊታዘዘው የሚገባ አንድ ሕግ ነበር። “መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ እንዳይበላ” አዘዘው። ሰው ይህን ትዕዛዝ ቢተላለፍ በእርግጥ እንደሚሞት እግዚአብሔር ተናገረ።<br>2. ሰው እንስሳትንና አእዋፍን የመሰየም ኃላፊነት ተሰጠው።<br>3. ሰው በኃላፊነቱ የምታግዘውን ረዳት እግዚአብሔር ፈጠረለት። በጋብቻ ወንድና ሴት አዲስ ቤተሰብ ይመሠርታሉ። እንደአንድ ቡድንም አብረው ይሰራሉ።<br>4. በእባብ የተመሰለው የእግዚአብሔር ጠላት ሰይጣን አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ እንዲጠራጠሩ አደረገ። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ቢተላለፉ እንደማይሞቱ ነገራቸው። እባብ ሴቲቱን አታለላት። እግዚአብሔር አትብሉ ካላቸው ፍሬም ወስዳ በላች። ለአዳምም ሰጠችው እርሱም በላ።<br>5. አዳምና ሔዋን ይህን ካደረጉ በኋላ ደስታቸውና ሰላማቸው ተወሰደባቸው። የበለስ ቅጠል ወስደው ልብስ እንዲሆናቸው አድርገው ሰፉት። ከለበሱትም በኋላ በቁጥቋጦ ውስጥ ተደበቁ። እግዚአብሔር ተጣራ። እነርሱም ያደረጉትን ነገሩት። አዳም በሔዋን አሳበበ። ሔዋን ደግሞ በእባቡ አሳበበች።<br>6. እግዚአብሔር እባቡን ረገመው። አዳምና ሔዋንም ለኃጢአታቸው የሚገባቸውን ቅጣት መቀበል ነበረባቸው። ሕመም መታመምና መታገል፣ እንዲሁም ከባድ ስራ መስራት ጀመሩ። ሕይወት ከበደችባቸው። አንድ ቀን ደግሞ ይሞታሉ።<br>7. እግዚአብሔር ከእንስሳት ቆዳ ለአዳምና ለሔዋን ልብስ አዘጋጀላቸው። የሕይወት ዛፍ እንዳይበሉም ከኤደን ገነት አስወጣቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ትምህርት ሶስትን አጠናቁ። | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br>ውይይትና ገለጻ<br><br>1. እግዚአብሔር ለሰው የኤደን ገነትን እንዲንከባከባና እንስሳትንና አእዋፍን የመሰየም ኃላፊነት ተሰጠው።<br>2. እግዚአብሔር ሰው ከሁሉም ዛፍ ፍሬ መብላት ይችላል። ሆኖም “መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ” መብላት እንደሌለበት ነገረው። ከዚህ ዛፍ ቢበላ ውጤቱ ሞት እንደሆነ ነገረው።<br>3. እግዚአብሔር ለሰው ረዳት ፈጠረለት። ሴት ብሎም ጠራት። በአንድ ላይ ሊሰሩ ይገባቸው ነበር። በጋብቻ ወንድና ሴት አዲስ ቤተሰብ ይመሠርታሉ። እንደአንድ ቡድንም አብረው ይሰራሉ።<br>4. ተንኮለኛው እባብ ሔዋን እግዚአብሔርን እንዳትታዘዝ አሳታት። ከተከለከለው የዛፍ ፍሬ በላች። ለአዳምም ሰጠችው። እርሱም በላ። እርሱም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላለፈ። አዳምና ሔዋን ከተከለከለው ዛፍ ፍሬ ስለበሉ እግዚአብሔር ካሰበላቸው ማንነት አንሰው ተገኙ።<br>5. አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መተላለፋቸው ገባቸው። ስለዚህም ሐፍረት ተሰማቸው። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የመተላለፍ ምርጫቸው ዋጋም መቀበል ነበረባቸው።<br>6. ከእግዚአብሔርም ቅጣታቸውን ተቀበሉ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ጥናት ሶስትን አጠናቁ። |
| ክለሳ | ይህን ትምህርት *ከሮሜ 5: 12 ጋር* አዛምዱት. አዳምና ሔዋን ባለመታዘዛቸው እኛ ሁላችን ኃጢአተኞች ሆነን ተወለድን። ተማሪዎቻችሁን በዚህ ዘመን እግዚአብሔርን የማንታዘዝባቸውን አንዳንድ ምሳሌዎችን እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። ይህ እንዴት ነው 1) በራሳችን ላይ 2) በሌሎች ሰዎች ላይ ተፅእኖ ማሳደር የሚችለው? | የአዳምና የሔዋን አለመታዘዝ ውጤቱ ምን ነበር? *ሮሜ 5: 12-14* እና *18-19* አንብቡ።<br>የአዳም አለመታዘዝ ዛሬ በእኛ ላይ ምን አስከተለ? |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ሁል ጊዜም እግዚአብሔር ይቅር እንዲለንና አዲስ እንዲያደርገን በሰራነው ስህተትና ኃጢአት መፀፀት አለብን። ያኔ በሕይወታችን ትዕዛዛቱን መፈፀምና እግዚአብሔርን ማስደሰት እንችላለን። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>እንደክርስቲያን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መፈፀም ለምን ያስፈልጋል? ዛሬ እግዚአብሔርን በተጨባጭ ልንታዘዝባቸው የምንችልባቸው መንገዶች ምንድናቸው? |

| | ሀ፣ – ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – ፍጥረት<br>ርዕስ – በእግዚአብሔር መንገድ ነገሮችን ማከናወን። | ሀ፣ – ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – ፍጥረት<br>ርዕስ – የኃጢአት ውጤት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት** : ***ዘፍጥረት 4: 1-16***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 14: 6***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. አቤል የእግዚአብሔርን መንገድ ተከተለ። ቃየን ደግሞ የራሱን መንገድ ተከተለ። እግዚአብሔር የአቤልን መስዋዕት ተቀበለ። የቃየንን መስዋዕት ግን አልተቀበለም።<br><br>2. ቃየን አቤልን ገደለ። እግዚአብሔር ካለበት ምድር አስወጥቶ ተቅበዝባዥ አደረገው። ቃየን ከእግዚአብሔር ሕልውና ርቆ ሄደ።<br><br>3. ለእግዚአብሔር አንድ መንገድ አለ። ያም መንገድ ደግሞ የእርሱ መንገድ ነው። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ዘፍጥረት 3: 7-24***<br><br>ቁልፍ ጥቅስ : *1 ቆሮንቶስ 15: 22; ሮሜ 6: 23*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ሞከሩ።<br>2. እግዚአብሔር አታላዩን እባብ ረገመው።<br>3. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን በኃጢአታቸው ምክንያት ሕመምን እንደሚታመሙና ከባድ ስራ በመስራት እነደሚኖሩ ነገራቸው።<br>4. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ራቁትነታቸውን የሚሸፍኑበትን ልብስ አዘጋጀላቸው።<br>5. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከኤደን ገነት አባረራቸው። . |
| መግቢያ | ያለካርታ ወይንም ደግሞ ያለአቅጣጫ ጉዞ ብትጀምሩ ምን ይከሰታል? በዚህ ምክንያት ጠፍታችሁ ታውቃላችሁ? ቃየን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ቸል ስላለ ተቅበዝባዥ ሆነ። | ተማሪዎቻችሁ በልጅነት እድሜያቸው በቤትወይንም በት/ቤት ታዛዥ ያልነበረቡትን እንዲያስታውሱና እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። በዚህስ ምን ተሰምቷቸው ነበር? |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>1. አዳምና ሔዋን ሁለት ልጆች ነበሯቸው። አቤል እረኛ ነበር። ቃየን ደግሞ ገበሬ ነበር።<br><br>2. እግዚአብሔር አቤል ያቀረበውን የእንስሳ መስዋዕት ተቀበለ። ይህም ከመንጋው በኩርና ምርጥ የሆነውን ጠቦት ነበር ለመስዋዕት ያቀረበው። እግዚአብሔር የቃየንን መስዋዕት አልተቀበለም። በዚህ ምክንያትም ቃየን ተከፋ፤ ደግሞም ተቆጣ።<br><br>3. እግዚአብሔር ቃየን በኃጢአት እንዳይሸነፍ ነገር ግን የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል እንዳለበት አስጠነቀቀው። ቃየን አልተፀፀተም። እግዚአብሔርንም አልሰማም።<br><br>4. ቃየን ወንድሙን አቤልን ገደለው። እግዚአብሔር ከዚያ ምድር አባረረው። ከእግዚአብሔር ሕልውናም ተለይቶ ተቅበዝባዥ ሆነ።<br><br>5. አቤል ለእግዚአብሔር የጠቦት መስዋዕት ማቅረብ እንዳለበት ያውቅ ነበር። ቃየን ግን እግዚአብሔር በመረጠው መንገድ ወደ እግዚአብሔር አልቀረበም። በዚህ ምክንያትም ተቀጣ።<br><br>6. የአቤል መስዋዕት የጌታ ኢየሱስ የመስቀል መስዋዕት ስዕል ነበር።.<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br>ውይይትና ገለጻ<br><br>1. የአዳምና የሔዋን አለመታዘዝ መልካምንና ክፉን የመለየት እውቀት እንዲሁም ራቁታቸውን የመሆናቸውን ግንዛቤ አስከተሉ። Adam and ስለፈሩ ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ፈለጉ።<br>2. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ጥያቄ ጠየቃቸው። ለፈፀሙት ስህተት ኃላፊነትን እንዲወስዱ ፈለገ። ሆኖም ሁለቱም ለፈፀሙት ስህተት በሌሎች ላይ አሳበቡ። አዳም ሔዋንን ሔዋን ደግሞ እባብን ለስህተታቸው ምክንያት አድርገው አቀረቡ።<br>3. አዳምና ሔዋን ያለመታዘዛቸውን መራራ ፍሬ ለመጎንጨት ተገደዱ። መታመም ጀመሩ፤ ሕይወት የትግል ሜዳ ሆነባቸው፤ በኤደን ገነት ካለው ከእግዚአብሔር ሕልውና ራቁ።<br>4. እኛም የኃጢአታችንን ፍሬ እንጎነጫለን። – አዳም ኃጢአትን ስለሰራ ከእረሱ ጋር በአንድ ላይ ተቆጥረናል። እኛም ልክ እንደእርሱ እንሞታለን።.<br>**5.** እግዚአብሔር የጸጋ አምላክ ነው። ለአዳምና ለሔዋን የእንስሳ ቆዳ ልብስ እንዲሆናቸውና እርቃናቸውን እንዲሸፍኑበት ሰጣቸው። ***ሮሜ 6: 23*** ጌታ ኢየሱስን እንደአዳኛችን ብንቀበል እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት በነጻ እንደሚሰጠን ያስተምርናል።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ጥናት አራትን አጠናቁት። |
| ክለሳ | በቁልፍ ጥቅሱ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ልንቀርብበት የምንችልበት ብቸኛ መንገድ ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚከተሏቸው ሌሎች መንገዶች ምንድናቸው?<br><br>ይህን ቁልፍ ጥቅስ በፖስት ካርድ ላይ አዘጋጁት። | በዚህ ትምህርት ስለእግዚአብሔር ባሕርይ ምን እንማራለን?<br><br>ይህን ትምህርት ከ***ሮሜ 5: 12*** ጋር አዛምዱት። አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስለተላለፉ እኛ ሁላችን ኃጢአተኞች ሆንን። በሕይወታችን እግዚአብሔርን የማንታዘዝባቸው ምሳሌዎችን ተማረዎቻችሁ እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። ይህ እንዴት ነው 1) በራሳችን ላይ 2) በሌሎች ሰዎች ላይ ተፅእኖ ማሳደር የሚችለው? |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?:**<br>ቁልፍ ጥቅሰን በቃላችሁ ያዙት።<br>ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበንን ብቸኛ መንገድ እየተከተልን ነውን? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?:**<br>እግዚአብሔር ትዕዛዙን ማክበር የሚያስችለንን ብርታት እንዲሰጠን ለምኑት።<br>እንዲሁም ስናሳዝነው በጸጋው ስለሚደግፈን አመስግኑት።<br>እግዚአብሔር ይቅር እንዲለንና አዲስ እንዲያደርገን በኃጢአታችን መፀፀት አለብን። ያኔ እግዚአብሔርን ለማስደሰትና ትዕዛዙን ለመፈፀም እንኖራለን። |

| | ሀ2 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – ኖህና የጥፋት ውኃ<br>ርዕስ – የመርከብ ግንባታ | ሀ2 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – ቃየንና አቤል<br>ርዕስ – እግዚአብሔርን ማምለክ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ዘፍጥረት 6: 5-22***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዘፍጥረት 6: 8***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። የሰዎች ኃጢአታኝነት የእግዚአብሔርን ልብ ሰበረው።<br>2. እግዚአብሔር ኖህን ለማዳን ወሰነ። እግዚአብሔር ኖህን፣ ቤተ ሰቡንና ከየእንስሳት ዝርያው ደግሞ ሁለት ሁሉቱን ያድን ዘንድ ደግሞ ትልቅ መርከብ እንዲገነባ አዘዘው።<br>3. ኖህ ልክ እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ። ኖህ እግዚአብሔርን አመነ ደግሞም ታዘዘው። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: *ዘፍጥረት 4: 1-16*<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: *ዕብራውያን 11: 4*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>1. አቤል እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ወደ እግዚአብሔር መጣ። እግዚአብሔርም የአቤልን መስዋዕት ተቀበለ።<br><br>2. ቃየን በራሱ መንገድ ወደ እግዚአብሔር መጣ። እግዚአብሔር መስዋዕቱን አልተቀበለውም። |
| መግቢያ | ለክፍሉ ተማሪዎች የግንባታ ሞዴል ወይንም ደግሞ የኬክ መጋገሪያ ቅደም ተከተል መመሪያ አሳዩቸው። አንድ ነገር ስንገነባ ወይንም ስንሰራ የግንባታውን የአሰራሩን ቅደም ተከተል መከተል በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ንገሯቸው። እግዚአብሔር ለኖህ ዝርዝር መመሪያ እንደሰጠውና ኖህም ይህን ዝርዝር መመሪያ እንደተከተለ ንገሯቸው። | መመሪያዎችን እንድንከተል የሚጠይቁ አንዳንድ ሁኔታዎችን ዘርዝሩ። ችላ ስንላቸው ምን ይገጥመናል? |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>1. በምድር ላይ የነበሩ ሰዎች እጅግ ክፉዎች ሆኑ። ኃጢአተኝነታቸውና አለመታዘዛቸው እግዚአብሔርን እጅግ በጣም አሳዘነው።<br>2. እግዚአብሔር የፈጠራቸውን እንስሳትና ሰዎችን በሙሉ ሊያጠፋቸው ወሰነ።<br>3. ኖህ ግን ልዩ ሰው ነበር። እግዚአብሔርን ያስደስት ነበር። ከሌሎች ሰዎች ሁሉ ልዩ የሚያደርገው ትክክለኛውን ነገር የሚያደርግና እግዚአብሔርን የሚወድና የሚታዘዝ ስለነበር ነው።<br>4. እግዚአብሔር ኖህን ሰዎችንና ሁሉንም ሕያዋን ፍጥረታት እንደሚያጠፋ ማስጠንቀቂያ ሰጠው። ምክንያቱም ምድርን በዓመፅ ሞልተዋት ነበርና ነው።<br>5. እግዚአብሔር ለኖህ ዝግጅት እንዲያደርግ ልዩ መመሪያን ሰጠው። እግዚአብሔር ኖህን፣ ቤተ ሰቡንና ከየእንስሳት ዝርያው ደግሞ ሁለት ሁሉቱን ያድን ዘንድ ደግሞ ትልቅ መርከብ እንዲገነባ አዘዘው።<br>6. ኖህ በእግዚአብሔር ታመነ። የተሰጠውን መመሪያ ልክ እግዚአብሔር እንዳለው ፈፀመ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን ማጠናቀቅ።** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br>ውይይትና ገለጻ<br><br>1. አዳምና ሔዋን ሁለት ልጆች ነበሯቸው። አቤል እረኛ ነበር። ቃየን ደግሞ ገበሬ ነበር።<br><br>2. እግዚአብሔር አቤል ያቀረበውን የእንስሳ መስዋዕት ተቀበለ። ይህም ከመንጋው በኩርና ምርጥ የሆነውን ጠቦት ነበር ለመስዋዕት ያቀረበው። እግዚአብሔር የቃየንን መስዋዕት አልተቀበለም። በዚህ ምክንያትም ቃየን ተከፋ፤ ደግሞም ተቆጣ።<br><br>3. እግዚአብሔር ቃየን በኃጢአት እንዳይሸነፍ ነገር ግን የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል እንዳለበት አስጠነቀቀው። ቃየን አልተፀፀተም። እግዚአብሔርንም አልሰማም።<br><br>4. ቃየን ወንድሙን አቤልን ገደለው። እግዚአብሔር ከዚያ ምድር አባረረው። ከእግዚአብሔር ሕልውናም ተለይቶ ተቅበዝባዥ ሆነ። .<br>5. አቤል ለእግዚአብሔር የጠቦት መስዋዕት ማቅረብ እንዳለበት ያውቅ ነበር። ቃየን ግን እግዚአብሔር በመረጠው መንገድ ወደ እግዚአብሔር አልቀረበም። በዚህ ምክንያትም ተቀጣ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>ጥናት አንድን አጠናቁ። |
| ክለሳ | ስለኖህ፣ ስለቤተ ሰቡና እግዚአብሔር ስለሰጠው መመሪያ የተማርነውን ትምህረርት በጥያቄዎች ከልሱት። | ቁልፍ ጥቅሱን አንብቡላቸው። ***ዕብራውያን 11: 4.*** ይህ ጥቅስ በአቤልና በቃየን መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት ነው ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርበው?? |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ኖህ በእግዚአብሔር አመነ። እናም እንዲያደርግ ያዘዘውን ሁሉ አደረገ። በእግዚአብሔር እንዴት እምነት ሊኖረን ይችላል? ታምኑታላችሁ? ኖህ በእግዚአብሔር አመነ። እግዚአብሔርም አዳነው። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ከአቤልና ከቃየን ሕይወትና ከአመለካከታቸው የምንማረው ትምህርት ምንድነው? እነኝህን የተማርናቸውን ትምህርቶች በሕይወታችን በተግባር ከዛሬ ጀምሮ ማሳየት የምንችለው እንዴት ነው? |

<table>
<tr><th></th><th>ሀ2 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – ኖህና የጥፋት ውኃ<br>ርዕስ – መርከብ ውስጥ ሲገቡ</th><th>ሀ2 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 - ሔኖክና ኖህ<br>ርዕስ – ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ</th></tr>
<tr><td></td><td>የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ዘፍጥረት 7: 1-20<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: ዘፍጥረት 7: 5<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>እግዚአብሔር ኖህና ቤተ ሰቡ የሚድኑበትን መንገድ አዘጋጀ።<br>ኖህ በእግዚአብሔር ታመነ። እግዚአብሔር ልክ እንደነገረውም አደረገ።</td><td>የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ዘፍጥረት 5: 21-33; ዘፍጥረት 6: 1-15<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: ዕብራውያን 11: 5<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>ሔኖክና የልጅ ልጁ አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር አደረጉ። ከእግዚአብሔር ጋርም ሕብረት ነበራቸው።<br>እነኝህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር በነበራቸው ግንኙነትና ሕብረት ምክንያት ከነበሩበት ማህበረሰብ ወጣ ያሉ ነበሩ።</td></tr>
<tr><td>መግቢያ</td><td>ከቤተ ሰቦቻችሁ ጋር ወደ አንድ ራቅ ወዳለ ቦታ ተጉዛችሁ ታውቃላችሁ? ለዚህ ጉዞ ያደረጋችሁት ዝግጅት ምን ይመስል ነበር?</td><td>ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ከሕዝቡ ሁሉ ለየት ያልን እንድንሆን ሊየደርገን ይገባል። ክርስቲያኖች ከሌሎች ሰዎች እንዴት ነው መለየት ያለባቸው? ዝርዝር አዘጋጁ።</td></tr>
<tr><td>ማጠናቀቅ</td><td>የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br>ውይይትና ገለጻ<br><br>እግዚአብሔር ከሰባት ቀናት በኋላ የጥፋት ውኃ እንደሚልክ ኖህን አስጠነቀቀው።<br>እግዚአብሔር ኖህን እንስሳትንም ወደ መርከቡ ይዞ እንዲገባ አዘዘው። ኖህ በዚህን ጊዜ የ600 ዓመት ነበር። ልክ እግዚአብሔር እንዳዘዘውም በ2ኛው ወር በ17ኛው ቀን ኖህ ቤተ ሰቡንና እንስሳቱን ይዞ ገባ።<br>ልክ እግዚአብሔር እንደተናገረው የጥፋት ውኃ ከሰባት ቀናት በኋላ መጣ።<br>ኖህ፣ ቤተ ሰቡና እንስሳቱ ሁሉ ወደ መርከቡ ከገቡ በኋላና ደህንታቸውን ካረጋገጠ በኋላ እግዚአብሔር የመርከቡን በር ዘጋው። ያን አስከፊ የጥፋት ውኃ ማምለጥ የቻሉት ኖህ፣ ቤተ ሰቡና በመርከቡ ውስጥ የነበሩት እንስሳት ብቻ ነበሩ። ዝናቡ ለ40 ቀናት መዝነቡን ቀጠለ። የውሃው ከፍታ ከመሬት 22 ጫማ ደረሰ። ትልልቅ ተራሮች ሳይቀሩ በውሃ ተሸፈኑ።<br><br>ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።<br>ትምህርት 2ን አጠናቁ። .</td><td>የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br>ውይይትና ገለጻ<br><br>ሔኖክ የኖረው 365 ዓመታት ነበር። በእድሜው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ነበረው።<br>መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን የሔኖክ አሟሟት እንደሌሎች ሰዎች አልነበረም። እግዚአብሔር ወደ ሰማይ ስለ ወሰደው ተሰወረ። አልተገኘም።<br>ኖህ ደግሞ የሔኖክ የልጅ ልጅ ነበር። እንደሄኖክ ኖህም ጻድቅ ሲሆን በሚኖርበት ማህበረሰብ ከሚኖሩት ክፉና በዓመጽ ከተሞሉት ሰዎች ጋር የማይወዳደር ሲሆን ከእግዚአብሔርም ጋር ሕብረት ነበረው።<br>በኖህ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ኃጢአተኝነት የእግዚአብሔርን ልብ ሰበረው። እነርሱን በጥፋት ውኃ ለመቅጣትና ኖህን ግን ለማዳን ወሰነ።<br>እግዚአብሔር መርከብ የሚሠራበትንና ቤተ ሰቡንና ራሱን የሚያድንበትን ዝርዝር መመሪያ ለኖህ ሰጠው።<br><br>ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።<br>ጥናት ሁለትን አጠናቁ።</td></tr>
<tr><td>ክለሳ</td><td>ፈጠራ ችሎታን መጠቀም! የኖህን፣ የቤተ ሰቡንና በመርከቡ ውስጥ የነበሩትን እንስሳት በውኃ ላይ ሲንሳፈፉ ስዕል ሳሉ። ለስዕሉም “እግዚአብሔር ያዳነቸው” የሚል ርዕስ ስጡት።</td><td>ሔኖክና ኖህ ምን አይነት ሰዎች ነበረ? ከሌሎች ሰዎች የሚለያቸው ምን ነበር?</td></tr>
<tr><td>ከሕይወት ጋር ማዘመድ</td><td>ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>እግዚአብሔር ኖህን ስለወደደው ከጥፋት ውኃ ለመዳን እንዲችል መንገድን አበጀለት። ኖህ በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መመሪያዎች መከተልና ተግባራዊ ማድረግ ነበር። እግዚአብሔር እኛም ለፍርድ ቀን ዝግጅት ማድረግ እንድናደርግ ይፈልጋል። በመስቀል ላይ እኛን ለማዳን ሲል በሞተው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንድናምን ይፈልጋል። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናችሁ ድናችኋል?</td><td>ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>መለስ ብላችሁ ክርስቲያኖችን በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውሰጥ ከሌሎች ሰዎች የሚለዩባቸውን ባሕርያት ዝርዝር እንገና እዩት። ቀጥላችሁም ሔኖክና ኖህ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አስቡ። በዚህ ሳምንት እግዚአብሔር በእርሱ ማመንና በመንገዶቹ መሄድ እንድትችሉ እንዲረዳችሁ ለምኑት። የአንድ ታማኝ ክርስቲያን ባሕርይን መርጣችሁ በዚህ ባሕርይ እግዚአብሔር እንዲያሳድጋችሁ ለምኑት።</td></tr>
</table>

| | ሀ2 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – ኖህና የጥፋት ውኃ<br>ርዕስ – በመርከቡ መዳን። | ሀ2 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – ኖህና የጥፋት ውኃ<br>ርዕስ – እግዚአብሔርን ማገልገል። |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ዘፍጥረት 8: 1-22*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ዘፍጥረት 8: 1*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>እግዚአብሔር ኖህንና ቤተ ሰቡን እንዲሁም በመርከቡ ውስጥ ያሉትን እንስሳት አሰበ። ተንከባከባቸውም።<br>አግዚአብሔር አድኖታልና ኖህ ውስጡ በምስጋና ተሞልቷል። እግዚአብሔር እንደገና ምድርን በጥፋት ውኃ እንደገና እንደማይመታ ቃልኪዳን አደረገ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ዘፍጥረት 6: 14-22; ዘፍጥረት 7: 1-24*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ዕብራውያን 11: 7*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>እግዚአብሔር ለኖህ የመርከብ ግንባታ ዝርዝር መመሪያ ሰጠው። ኖህም ይህን የእግዚአብሔር መመሪያ ልክ እግዚአብሔር እንደተናገረው አድርጎ በመታዘዙ ዳነ። |
| *መግቢያ* | ቤተ ሰቦቻችሁ፣ ወዳጆቻችሁ ወይንም መምህራኖቻችሁ እንንተን የሚንከባበከቡበትን መንገድ ዘርዝሩ።<br>እግዚአብሔር በየቀኑ እኛን እንዴት እንደሚንከባከበን ዘርዘሩ።<br>የቤተ ሰቦቻችን አባላትን፣ ወዳጆቻችንንና መምህራንን ለሚያደርጉልን እንክብካቤና ማናቸውም ነገር ማመስገን እንዳለባቸው የክፍሉን ተማሪዎች አሳስቧቸው። ከዚህ ባላነሰ መልኩ ስናምንበት እኛን የሚያድነን እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል። | በመርከብ ወይንም በአውሮፕላን ውስጥ ስላሉ የደህንነት መመሪያዎች ከክፍሉ ተማሪዎች ጋር ተወያዩባቸው። ሰዎች ትኩረት ይሰጧቸዋል? ለምን? ኖህ እግዚአብሔር የሰጠውን መመሪያ ማክበር ለምን አስፈለገው? |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>እግዚአብሔር ኖህን፣ ቤተ ሰቡንና በመርከቡ ውስጥ የነበሩትን እንስሳት አሰበ። በምድር ላይ ንፋስን ላከ። የውኃውም መጠን እየቀነሰ መጣ።<br>ከአንድ መቶ አምሳ ቀናት ወይንም ደግሞ ከአምስት ወራት በኋላ መርከቢቱ በአራራት ተራራ ላይ አረፈች። ከዚያም ከተጨማሪ ሁለት ወራት በኋላ ውኖቹ መጠናቸው እየቀነሰ መጣ። ተጨማሪ ተራሮችም መታየት ጀመሩ።<br>ከ40 ቀናት በኋላ ኖህ የመርከቡን መስኮት ከፍቶ ቁራን ላከ። ቁራ ግን ተመልሶ አልመጣም። ከዚያም እርግብን ላከ። እርግቢቱ የምታርፍበት መሬት ስላላገኘች ተመልሳ መጣች። ከሰባት ቀናት በኋላ ደግሞ እንደገና እርግብን ላከ። ታዲያ በዚህ ጊዜ እርግቢቱ የወይራ ዛፍ ቅጠል ይዛ ተመለሰች። በዚህም ኖህ ውኃው መጉደሉን ተረዳ። እንደገና ከሰባት ቀናት በኋላ እርግብን ላካት። እርግብ ግን ተመልሳ አልመጣችም። በአጠቃላይ ከአስራሁለት ተኩል ወራት በኋላ መሬት ደረቀች።<br>እግዚአብሔር ኖህ ከቤተ ሰቦቹና ከእንስሳቱ ጋር ከመርከቡ ውስጥ እንዲወጣ ነገረው።<br>ኖህ በምስጋና ተሞላ። ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መስዋዕት የሚያቀርብበት መሰዊያ ሰራ።<br>እግዚአብሔር በኖህ መስዋዕት ደስ ተሰኘ። ሕያዋን ፍጥረታትን እንደገና እንደማያጠፋቸው ቃል ገባለት።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**Complete ትምህርት 3.** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>እግዚአብሔር ለኖህ ትልቅ መርከብ ለመገንባት የሚያስችለውን ዝርዝር መመሪያ ሰጠው። ይህም እግዚአብሔር ሊልከው ላለው ትልቅ የጥፋት ውኃ ኖህን ለማዘጋጀት አስቦ ነው።<br>እግዚአብሔር የጥፋት ውኃን አስመልክቶ በዝርዝር አስጠንቅቆታል። እግዚአብሔር ኖህን፣ ቤተ ሰቡንና እንስሳቱን ለማዳን ቃል ኪዳን ገባለት።<br>እግዚአብሔር እንስሳቱን ለማዳን የሚያስችለውን ዝርዝር መመሪያ ለኖህ ሰጠው። ኖህ፣ ቤተ ሰቡና እንስሳቱ ወደ መርከቡ ውስጥ ገቡ። እግዚአብሔርም ሁሉም ከገቡ በኋላ መርከቡን ከውጭ ዘጋባቸው።<br>የጥፋት ውኃ የቆየው ለ40 ቀናት ሲሆን ከመርከቡ ውጪ የነበረ ሕያው ፍጥረት ሁሉ ከዘነበው ከባድ ዝናብ የተነሳ ጠፋ። ኖህ፣ ቤተ ሰቡና በመርከቡ ውስጥ የነበሩ እንስሳት ብቻ ዳኑ። በውኖችም ላይ እንዲንሳንፈፉ በማድረግ ጥበቃ አደረገላቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ፖስተር አዘጋጁ። በፖስተሩም ላይ እግዚአብሔርን የምናመሰግንባቸውን ነገሮች ዝርዝር ጻፉ። ከእነኝህ መካከል ዋነኛው መዳናችን ነው። | በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለ እግዚአብሔርና ስለኖህ የምንማራቸው ባሕርያት ምንድናቸው? ሁለቱንም መግለፅ የሚችሉ ቃላትን ዝርዝር አዘጋጁ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>እግዚአብሔር ኖህን አዳነው። እንዲሁም ተንከባከበው። እግዚአብሔር እኛንም ሊያድነንና ሊንከባከበን ይችላል። ልንታመንበትና ልናመሰግነው ይገባናል። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ቁልፍ ጥቅሱን አንብቡላቸው። በሕይወታችን ኖህ እንዴት ምሳሌ ሊሆንልን ይችላል? በዙሪያችን ባሉ ሰዎች ላይ ይህ ምን ተፅእኖ ሊፈጥር ይችላል? |

<table>
<tr><th></th><th>ሀ2– ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – ኖህና የጥፋት ውኃ<br>ርዕስ – ሕይወት ከመርከብ ውጪ</th><th>ሀ2 – ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – ኖህና ቤተ ሰቡ<br>ርዕስ – እግዚአብሔርን ማምለክ።</th></tr>
<tr><td></td><td>የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ዘፍጥረት 9: 7-17<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: ዘፍጥረት 9: 15<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>እግዚአብሔር ከኖህ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። ከአሁን በኋላ ሕያዋን ፍጥረታትን በጥፋት ውኃ እንደማያጠፋቸው ቃል ገባ። የዚህ ቃል ኪዳን መታሰቢያ እንዲሆንም እግዚአብሔር በሰማይ ላይ ቀስተ ደመናን አደረገ።.</td><td>የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ዘፍጥረት 8: 1-22; ዘፍጥረት 9: 11-16<br><br>ቁልፍ ጥቅስ: ኤፌሶን 2: 8<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>እግዚአብሔር ኖህን፣ ቤተ ሰቡንና በመርከቡ ውስጥ ያሉ እንስሳትን አስታወሳቸው።<br><br>ኖህ በምስጋና ተሞላ። ከመርከቡ ውስጥ ከወጣ በኋላም ምንም ነገር ከማድረጉ በፊትም እግዚአብሔርን አመለከ። እግዚአብሔርም የምድርን ነዋሪዎች እንደገና በውኃ ጥፋት እንደማያጠፋ ቃል ገባለት።</td></tr>
<tr><td>መግቢያ</td><td>በጥንድ በጥንድ ሰዎች ስለሚገቧቸው የተለያዩ ቃልኪዳኖች ተወያዩ። ሰዎች የገቡትን ቃል ሁልጊዜ ይፈጽማሉ?</td><td>በጥንድ ሆነው ስለ ምስጋና ካርዶችና ስጦታዎች እንዲወያዩ አድርጓቸው። ለምንድነው ሰዎች እነኝህን ለሌሎች ሰዎች የሚልኩት? እናንተስ ልካችሁ ታውቃላችሁ? ለምን?</td></tr>
<tr><td>ማጠናቀቅ</td><td>የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br>ውይይትና ገለጻ<br><br>እግዚአብሔር ኖህንና ቤተ ሰቡን እንዲባዙና ምድርን እንዲሞሉ ነገራቸው።<br>እግዚአብሔር ምድርንና በውስጧ ያሉትን ፍጥረታት በሙሉ በጥፋት ውኃ እንደገና እንደማያጠፋት ቃል ኪዳንን አደረገ።<br>እግዚአብሔር በደመናዎች መካከል የሚታይ ቀስተ ደመናን ለቃል ኪዳኑ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ አደረገ። እግዚአብሔር በፍጹም ቃል ኪዳኑን አይረሳም።<br><br>ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።<br>ትምህርት አራትን አጠናቁ።</td><td>የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br>ውይይትና ገለጻ<br><br>እግዚአብሔር የትልቅ መርከብ ግንባታ ዝርዝር መመሪያ ሰጠው። ይህም ሊልክ ላለው ትልቅ የውኃ ጥፋት ኖህን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ነው።<br>እግዚአብሔር ኖህን፣ቤተ ሰቡንና በመርከቡ ውስጥ የሚገቡትን እንስሳት ለማዳን ቃል ገባለት።<br>አስፈሪው የጥፋት ውኃ መጣ። ለአርባ ቀናጽም ቆየ። ኖህ፣ ቤተ ሰቡና በመርከቡ ውስጥ የነበሩት እንስሳት ብቻ ዳኑ።<br>ዝናቡ አቆመ። ውኖቹም መጠናቸው እየጎደለ መሄድ ጀመረ። መርከቢቱም በአራራት ተራራ ላይ አረፈች።<br>ከአርባ ቀናት በኋላ ኖህ ቁራን ከመርከቡ ውጪ ላከው። ውኃው ሙሉ በሙሉ እስኪደርቅ ድረስ በምድር ላይ ከወዲህ ወዲያ ትበር ነበር።<br>ከዚያም እርግብን ላከ። ደረቅ መሬት ስላላገኘት ተመልሳ መጣች።<br>ከሰባት ቀን በኋላም ኖህ መልሶ እርግቢቱን ላካት። ይሄኔ የወይራ ዛፍ ቅጠል በአፏ መጣች። እንደገና ከላካት በኋላ ግን ተመልሳ አልመጣችም። መሬት እየደረቀች በሄድ ላይ ነበረች።<br>እግዚአብሔር ኖህን ከቤተ ሰቡ ጋር ከመርከቡ ውስጥ እንዲወጣ እንዲበዛና ምድርን እንዲሞላ ነገረው። ከመርከቡ ውስጥ እንደወጣ ኖህ ያደረገው የመጀመሪያው ነገር ለእግዚአብሔር መሰዋት ነበር።<br>እግዚአብሔር ከኖህ፣ ከልጆቹና ከሌሎቹ የቤተ ሰቡ አባላት ጋር እንዲሁም በምድር ላይ ከነበሩ ሕያዋን ፍጥረታት ጋር ልዩ ቃል ኪዳንን አደረገ።<br>እግዚአብሔር ምድርንና በውስጧ ያሉትን ፍጥረታት በሙሉ በጥፋት ውኃ እንደገና እንደማያጠፋት ቃል ኪዳንን አደረገ።<br>እግዚአብሔር በደመናዎች መካከል የሚታይ ቀስተ ደመናን ለቃልኪዳኑ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ አደረገ። እግዚአብሔር በፍጹም ቃል ኪዳኑን አይረሳም።<br><br>ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።<br>ጥናት አራትን አጠናቁ።</td></tr>
<tr><td>ክለሳ</td><td>ፈጠራ ችሎታን መጠቀም! ቀስተ ደመናን የያዘ ፖስተር አዘጋጁ። ርዕሱም “እግዚአብሔር ለዘላለም ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል” የሚል ይሁን።</td><td>በቡድን ውይይቶች ከተካሄዱ በኋላ ግብረ መልስ ለሁሉም ክፍል ይሰጥ። በዚህ ክፍለ ጊዜ ስለአምልኮ ምን ተማርን?</td></tr>
<tr><td>ከሕይወት ጋር ማዘመድ</td><td>ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>ለኖህ እግዚአብሔር የገባለት ቃል ኪዳን ዘላለማዊ ነበር። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ለዘላለም ይጠብቃል። ይህ በሕይወታችን ምን አይነት ለውጥ ማምጣት አለበት?</td><td>ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>ኖህ እግዚአብሔር ባደረገለት ነገር በምስጋና ተሞልቷል። እግዚአብሔር በሕይወታችን ላመጣቸው በረከቶች ምስጋናችንን በተጨባጭ የምንገልጽባቸው መንገዶች ምንድናቸው?</td></tr>
</table>

| | ሀ3 - ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 - የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ - ኢየሱስ ጴጥሮስን ጠራው። | ሀ3 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1 - የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ - ጥሪው |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ማቴዎስ 4: 17-22*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ማቴዎስ 4: 19*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ኢየሱስ ሰዎች እንዲከተሉት ጥሪ ያርብላቸዋል።<br><br>ኢየሱስን መከተል ማለት በእርሱ ማምንና ንስሐ መግባት እንዲሁም ከኃጢአት መራቅ ማለት ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ማቴዎስ 4: 17-22 ዮሐንስ 1: 35-42*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ማቴዎስ 4: 19*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ኢየሱስን መጀመሪያ የተገናኙት ምናልባት እንድርያስና ዮሐንስ ናቸው።<br>ከጥቂት ጊዜ በኋላም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሆኑ።<br>ኢየሱስ መሲህና አዳኝ መሆኑን አወቁ። |
| መግቢያ | በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ወይንም ደግሞ በሌሎች ፕሮጀክቶች ውስጥ ሲሳተፉ አብሯቸው የሚሰራ ቡድን የማስፈለጉን እውነት አውሩበት።<br>ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን መጀመሩ ነው። እናም እርሱ ከሄደ በኋላ ስራውን የሚቀጥሉ ሰዎችን ማሰልጠን ያስፈልገው ነበር። | ሰዎች የአንድ እግር ኳስ ቡድን ወይንም ደግሞ የአንድ ታዋቂ ድምጻዊ ደጋፊዎች ወይን ተከታዮች እንዴት እንደሚሆኑ አውሩ።<br>ሰዎች የኢየሱስ ተከታዮች የሆኑት ባሕርዩን አይተውና የሚናገራቸውን ቃላት ሰምተው እንደነበር ግለጹላቸው።<br>ኢየሱስም የተወሰኑ ሰዎች ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ ጥሪ እንዳቀረበላቸው ግለጹላቸው። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ኢየሱስ የሰበከው መልእክት (*4: 17*)<br><br>ኢየሱስ ዮሐንስና ጴጥሮስ መረባቸውን ሲጥሉ አያቸው።<br>ኢየሱስ በቡድን አብረው ይሰሩ የነበሩ ብርቱ አሳ አጥማጆችን ለአገልግሎት ጠራቸው። ስራውን ለመስራት መሰልጠን እንደሚችሉ ያውቅ ነበር።<br>ለእርሱ ጥሪ የሰጡት ፈጣን በታዛዥነት የተሞላ ምላሽ ነበር።።<br>ኢየሱስ ዮሐንስንና ያዕቆብንም ጠራቸው። እነርሱም ለጥሪው ወዲያው ታዘዙ።<br>እነኝህ የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ናቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ዮሐንስ መጥምቁ ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ ነው አለ። እንድርያስና ጓደኞቹ ደግሞ ኢየሱስ መሲሁ እንደሆኑ ተረዱ። *(ዮሐንስ 1: 35, 41)*<br><br>እንድርያስ ጴጥሮስን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የማስተዋወቁ ጠቀሜታ።<br>በኋላ ኢየሱስ አሳ በማጥመድ ላይ ሆነው ሲያገኛቸው ተከታዮቹ እንዲሆኑ ጥሪ አቀረበላቸው። እነርሱም ወዲያው ለመከተል መወሰናቸው የሚያስደንቅ አይደለም።<br>የእንድርያስ የግል ምስክርነቱ ምሳሌ።<br>የኢየሱስ ክርስቶስ የግል ልምምድ ለሌሎች ይህን የመንገር አስፈላጊነት<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ***ለተማሪዎቻችሁ ጥያቄዎች***<br>ኢየሱስ እነኝን ሰዎች ለምን ለይቶ ጠራቸው?<br><br>በዚህ ባለንበት ዘመን ለእግዚአብሔር ጥሪ መታዘዝ ምን ማለት ነው?<br><br>በዚህ ዘመን ለእግዚአብሔር ጥሪ መታዘዝን ከባድ የሚያደርጉ ነገሮች ምንድናቸው?<br>ጌታ ኢየሱስ ምን ቃል ገባላቸው? *(See 4: 19)* | ***ለተማሪዎቻችሁ ጥያቄዎች***<br>እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ ልዩ ዓላማ እንዳለው እንዴት ታውቃላችሁ?<br>ለእነኝህ የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ምን እቅድ ነበረው?<br>የእግዚአብሔርን እቅድ ማወቃችን ጥቅሙ ምንድነው?<br>እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን አላማ የምንረዳው እንዴት ነው?<br>እንዴትስ ለዚህ የእግዚአብሔር አላማ ምላሽ እንሰጣለን? |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ዛሬ የመዳን ቀን ነው በሚለው ሀሳብ ላይ ተወያዩ።<br>የንስሐ ጸሎት ጻፉ። በቅርጫት ውስጥ ከተቱት።<br>የታወቁ ክርስቲያኖችን የአገልግሎት ጥሪ በተመለከተ ጥናት አካሂዱ። ለምሳሌ የዴቪድ ሊቪንግስተን። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>**ዛሬ ስለ እግዚአብሔር መልካምነት ለሌሎች ልንነገር ስለምንችልባቸው አጋጣሚዎች ተወያዩባቸው።**<br>የኢየሱስ ክርስቶስን የተወሰኑ ስሞችና ማዕረጎች አውሩባቸው። |

| | ሀ3- ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 - የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ - መጠነ ሰፊው አሳ ማጥመድ | ሀ3 ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ - ተግዳሮቶቹ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ሉቃስ 5: 1-11*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ሮሜ 3: 23*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን መታዘዝ እንዳለባቸው ተማሩ።<br><br>ኢየሱስ ታላቅና ኃያል ነው። ድንቅና ተአምራት ማድረግ ይችላል።<br><br>እግዚአብሔር ንስሐ የሚገባን ማንንም ሰው መጠቀም ይችላል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ማቴዎስ: 14: 22-33*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ማቴዎስ 14: 33*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ተማሩ። እንዲሁም ፍርሃትን ሙሉ በሙሉ መንቀል እንደሚችል ተማሩ። በኢየሱስ ማመን በሕይወታችን የሚከሰቱ ማዕበላትን እንድናሸንፍ ያስችለናል። |
| መግቢያ | በት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በተገቢው መንገድ ተከታተለው እንደሆነ ለማረጋገጥ በተደጋጋሚ ቴስቶች(ሙከራዎች) ወይንም ፈተናዎች እንደሚሰጡ አውሩ።<br>በዚህ አሁን በምናየው አጋጣሚ ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እምነትና መታዘዝ ለፈተና ሲያጋልጠው እንመለከታለን። | ሕይወታችን በውልደታችን ጊዜ ተጀምሮ እስከእለተ ሞታችን ድረስ በሚቀጥል ጉዞ እንደሚመሰል ግለጹላቸው። በዚህ ጉዞ አንዳንዴ ነገሮች ቀላልና ለጥ ያለ ሜዳ የሚሆኑበት ጊዜ አለ። በሌላ ጊዜ አባጣ ጎርባጣ የሚበዛባቸው ማዕበላማ ጊዜዎችም አሉ። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይናገር የነበረው በጴጥሮስ ጀልባ ላይ ሆኖ ነበር።<br><br>ለሕዝቡ ተናግሮ ሲጨርስም እንደገና አሳ ማጥመዳቸውን እንዲቀጥሉ ነገራቸው።. (ሌሊቱን በሙሉ ሲያጠምዱ አድረዋል። ከፍተኛ ድካም ነበረባቸው። እንዲሁም ተርበዋል። ከዚያ በላይ ደግሞ ምን አሳ አልያዙም።)<br><br>ጴጥሮስ ኢየሱስ እንዳዘዘው አደረገ። እጅግ በጣም ብዙ አሳም አጠመዱ።<br><br>ጴጥሮስ ኢየሱስ ታላቅ መሆኑንና እርሱ ደግሞ ትንሽ መሆኑን ተገነዘበ! ***(ቁጥር 8)***<br><br>ደቀ መዛሙርቱ ሁሉን ትተው ኢየሱስን ተከተሉት።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br><br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>ኢየሱስ ትልቅ ተአምርን አደረገ። ደቀ መዛሙርቱን ከገሊላ ባሕር ባሻገር አልፈው እንዲጠብቁት ነገራቸው።<br><br>ወደ ተራራ ለመጸለይ ሄደ።<br><br>ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ እየተጓዙ እያለ ኃይለኛ ማዕበል አገኛቸው።<br><br>ኢየሱስም ይህን አውቆ በውኃ ላይ እየተራመደ ወደ እነርሱ መጣ።<br><br>ጴጥሮስም በውኃው ላይ እየተራመደ ወደ ኢየሱስ እንዲመጣ ጠየቀው። ኢየሱስም ፈቀደለት። በውኃ ላይም እየተራመደ ወደ ኢየሱስ ሄደ።<br><br>መስጠም ጀመረ። ኢየሱስ እንዲያድነው ተጣራ። ኢየሱስም አዳነው።<br><br>በኢየሱስ መታመን ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጹላቸው።<br>በኢየሱስ ስንታመን በሕይወታችን በሚገጥሙን ማዕበላት ሊረዳን እንደሚችል ግለጹላቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | **ለተማሪዎቻችሁ ጥያቄዎች**<br>በቁጥር 5 ላይ የስምዖን ጴጥሮስ ምላሽ ምን ማለት ነው?<br>ከጴጥሮስ ንስሐ ምን ትምህርት እንማራለን?<br>ንስሐ መግባት ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩበት።<br>ስለ ኢየሱስ "ሁሉን መተው" እንዴት እንችላለን? | **ለተማሪዎቻችሁ ጥያቄዎች**<br><br>በቁጥር 27 ላይ ያለው የኢየሱስ ቃል እንዴት ያበረታታናል?<br><br>ከጴጥሮስ ምሳሌ ምን እንማራለን?<br><br>በሕይወታችን ከሚገጥሙን ማዕበላት ምን ልንማር እንችላለን? |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ከፊት ለፊታችሁ ባለው ሳምንት ኢየሱስን የምትታዘዙባቸው ሶስት መንገዶች ጥቀሱ።<br>በሕይወቱ ስለ እግዚአብሔር ይቅርታ በሚገባ የተገነዘበበትን አንድ ጊዜ አስታውሶ ሊነግራችሁ የሚችል አንድ የምታውቁትን ክርስቲያን ጠይቁ። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>በሕይወታችሁ ገጥሟችሁ ስለሚያውቅ አንድ ማዕበል በቡድን ተወያዩ። በዚህ ሁኔታ ውስጥም በኢየሱስ በመታመናችን እንዴት እንደረዳን እንነጋገር።<br><br>ኢሳያስ ***43: 2*** ን አንብቡ። ኢየሱስን ለሚከተሉ ይህን አስቡ። ይህ ጥቅስ እንዴት ነው ከዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን ጋር የሚዛመደው? |

| | ሀ3 ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ - ኢየሱስ ጴጥሮስን አዳነው። | ሀ3 ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ - የጴጥሮስ ኑዛዜ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ማቴዎስ 14: 22-33*<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ማቴዎስ 14: 33*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።<br>በኢየሱስ ማመን በዘመናችን የሚገጥሙንን የሕይወት ማዕበላትና ፍርሃቶቻችንን እንድናሸንፍ ይረዳናል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ማቴዎስ 16: 23-28*<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ሮሜ 10: 9*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ኢየሱስ "ክርስቶስ" ወይንም "መሲሁ" ነው።<br>ጴጥሮስ ለኢየሱስ የሰጠው ምላሽ ለቤተ ክርስቲያን መሠረት ሆነ። |
| መግቢያ | ስለ ሕይወት ጉዞ አውሩ። ሕይወታችን በውልደታችን ጊዜ ተጀምሮ እስከእለተ ሞታችን ድረስ በሚቀጥል ጉዞ እንደሚመሰል ግለጹላቸው። በዚህ ጉዞ አንዳንዴ ነገሮች ቀላልና ለጥ ያለ ሜዳ የሚሆኑበት ጊዜ አለ። በሌላ ጊዜ አባጣ ጎርባጣ የሚበዛባቸው ማዕበላማ ጊዜዎችም አሉ። | ሰዎች ሊመልሱት የሚገባ ትልቅ ጥያቄ በኢየሱስ ማንነት ዙሪያ የሚጠየቀው ጥያቄ እንደሆነ ተነጋገሩበት።<br>ኢየሱስ በምድር ይመላለስ በነበረበት ወቅት ሰዎች ኢየሱስ ማን እንደሆነ ሲጠይቁ የተለያዩ መልሶች ይሰጣቸው ነበር። ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን እርሱ ማን እንደሆነ ጠየቃቸው። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br><br>ኢየሱስ ትልቅ ተአምርን አደረገ። ደቀ መዛሙርቱን ከገሊላ ባሕር ባሻገር አልፈው እንዲጠብቁት ነገራቸው።<br><br>ወደ ተራራ ለመጸለይ ሄደ።<br><br>ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ እየተጓዙ እያለ ኃይለኛ ማዕበል አገኛቸው።<br><br>ኢየሱስም ይህን አውቆ በውኃ ላይ እየተራመደ ወደ እነርሱ መጣ።<br><br>ጴጥሮስም በውኃው ላይ እየተራመደ ወደ ኢየሱስ እንዲመጣ ጠየቀው። ኢየሱስም ፈቀደለት። በውኃ ላይም እየተራመደ ወደ ኢየሱስ ሄደ።<br><br>መስጠም ጀመረ። ኢየሱስ እንዲያድነው ተጣራ። ኢየሱስም አዳነው።<br><br>*በኢየሱስ መታመን ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጹላቸው።*<br>*በኢየሱስ ስንታመን በሕይወታችን በሚገጥሙን ማዕበላት ሊረዳን እንደሚችል ግለጹላቸው።*<br>*አስቸጋሪ በሆኑ ጊዜያት በኢየሱስ የማመን አስፈላጊነትን አስቡ።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>1. **ትምህርት ሶስትን አጠናቁ** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>ኢየሱስ አሁን የሚገኘው በሰሜናዊ ጫፍ የአገልግሎት ጉብኝት እያደረገ ነው። (በዚህ ጥናት ያለውን ካርታ ተመልከቱ።)<br><br>"ሰዎች እኔን ማን ነኝ ይላሉ?" ሲል ደቀ መዛሙርቱን ይጠይቃቸዋል። - ለዚህ ጥያቄ የተሰጡ አራት ምላሾችን ልብ በሏቸው።<br><br>ከዚያም "እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?" ሲል ይጠይቃቸዋል።<br><br>የጴጥሮስን ፈጣን ምላሽ አስተውሉ።<br><br>ኢየሱስም እርሱ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያምኑ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚመሰርቱ ገለጸላቸው። ሕንጻ አይደለም። የአማኞች ስብስብ እንጂ!<br><br>ኢየሱስ በመቀጠልም እንደሚሞትና ከሙታን እንደሚነሳ ገለጸላቸው።<br><br>ጴጥሮስ ግን ይህ አይሁን አለ። ኢየሱስ ለዚህ የጴጥሮስ አባባል የሰጠውን ምላሽ አስተውሉ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br><br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ***ለተማሪዎቻችሁ ጥያቄዎች***<br>ኢየሱስ ፍርሃታችንን እንድንጋፈጥ እንዴት ይረዳናል?<br><br>ወጣቶች የሚገጥሟቸውን የተለመዱ ችግሮች ጥቀሱ።.<br><br>ይህ ክፍል እንዴት ይረዳናል? | ***ለተማሪዎቻችሁ ጥያቄዎች***<br>የእግዚአብሔር ወገኖች መሆናችንን እንዴት ነው እርግጠኞች ትሆናላችሁ?<br><br>የቤተ ክርስቲያን አካል የምንሆነው እንዴት ነው?<br><br>የቤተ ክርስቲያን አካላት የመሆናችን ጥሩ ነገሮች ምንድናቸው? |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | በግድግዳ ላይ የሚለጠፍና የሚታይ የችግሮች ዝርዝር አዘጋጁ። ከዚያም እነኝህን ችግሮች በመስቀሉ ላይ ጠርቋቸው።<br>ቀስተ ደመና ሳሉ። ከዚያም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ቃል ኪዳን ወስዳችሁ በላዩ ላይ ጻፉበት። | ስለቤተ ክርስቲያናችሁ እግዚአብሔርን በግላችሁ የምታመሰግኑበትን ነገር አስባችሁ ጻፉት። ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የምትነግሩት አንድ ሰው አስቡ። |

| | ሀ3 ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ - ኢየሱስ ማነው? | ሀ3 ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ - በተራራው ላይ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ማቴዎስ 16: 13-23***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ሮሜ 10: 9***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መመስከር አለብን።<br><br>2. ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***ማቴዎስ 17: 1-13***<br>**ቁልፍ ጥቅስ :** ***2 ጴጥሮስ 1: 16-18***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>1. ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ልዩ ነው።<br><br>2. ኢየሱስ ከሙሴም ሆነ ከኤልያስ ይበልጣል። |
| *መግቢያ* | ዝነኛ ስለሆኑ ሰዎች አውሩ። እነኝህ ሰዎች ለምን ዝነኛ እንደሆኑ አስቡ። ኢየሱስ ዝነኛ ሆነ። ሆኖም ብዙ ሰዎች ማን እንደሆነ አያውቁም ነበር። | ተማሪዎቻችሁ በፍጹም የማይረሱትን ገጠመኛቸውን እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። ሶስቱ ደቀ መዛሙርት በተራራው ላይ ያዩትን የኢየሱስን እውነተኛ ክብር እንደማይረሱት ግለጹላቸው። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት። :**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>✓ “ሰዎች እኔን ማን ነኝ ይላሉ?” ሲል ደቀ መዛሙርቱን ይጠይቃቸዋል። - ለዚህ ጥያቄ የተሰጡ አራት ምላሾችን ልብ በሏቸው።<br><br>✓ ከዚያም “እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?” ሲል ይጠይቃቸዋል።<br><br>የጴጥሮስን ፈጣን ምላሽ አስተውሉ።<br><br>✓ የጴጥሮስን ምላሽ አሰፈላጊነትና ለአማኞች ምን ማለት እንደሆነ ግለጹላቸው።<br><br>✓ ኢየሱስም እርሱ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የሚያምኑ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚመሰርቱ ገጸላቸው። *ሕንጻ አይደለም። የአማኞች ስብስብ እንጂ!*<br><br>✓ ኢየሱስ በመቀጠልም እንደሚሞትና ከሙታን እንደሚነሳ ገለጸላቸው።<br><br>✓ ጴጥሮስ ግን ይህ አይሁን አለ። ኢየሱስ ለዚህ የጴጥሮስ አባባል የሰጠውን ምላሽ አስተውሉ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>✓ **ትምህርት አራትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሶስቱን ይመርጥና ከእርሱ ጋር ወደ አንድ ተራራ አብረውት እንዲጓዙ አደረገ።<br><br>በሙሉ ክብሩና ንግስናው ከሙሴና ከኤልያስ ጋር ተገለጠ።<br><br>ጴጥሮስ ሶስት ድንኳኖችን ሰርቶላቸው በዚያ መቆየት ፈለገ።<br><br>እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ሰው ይልቅ እንደሚበልጥ ሊያስታውሳቸው ፈልጎ ከሰማይ ተናገረ።<br><br>ደቀ መዛሙርቱ ፈሩ። ጌታ ኢየሱስ ግን አጽናናቸው። ምን እንደሆነም ገለጸላቸው።<br><br>ኢየሱስ ልዩ መሆኑንና እንዴትም አስደናቂ ሰው እንደሆነ ግለጹላቸው።<br><br>በሕይወታችን ቀዳሚ ስፍራ የመስጠት አስፈላጊነትን እንዲያስቡ ጠይቋቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ***ለተማሪዎቻችሁ ጥያቄዎች***<br>***በቁጥር 22*** *ላይ ያለው የጴጥሮስ ቃላት ለምንድነው ስህተት የሚሆኑት?*<br><br>እግዚአብሔርን በተሻለ መንገድ እንድናገለግለው ቤተ ክርስቲያናችን እንዴት ልትረዳን ትችላለች?<br><br>በእውነት ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለሌሎች የምንናገር ጥሩ ምስክሮች መሆን የምንችለው እንዴት ነው? | ***ለተማሪዎቻችሁ ጥያቄዎች***<br><br>ጴጥሮስ የተለወጠውን ኢየሱስ ማየቱ የሚያስፈልገው ለምንድነው ትላላችሁ?<br><br>ከዚህ ልምምድ ደቀ መዛሙርቱ ምን ተማሩ ትላላችሁ?<br><br>በሕይወታችን ቀዳሚውን ስፍራ ለኢየሱስ መስጠት የምንችለው እንዴት ነው? |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | በግድግዳው ላይ የሚታይ የቤተ ክርስቲያን ስዕል ስሩ። ከዚያም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለ ቤተ ሰብ አባል የመሆን ጥቅሞችን ዘርዝሩ።<br>ልትመሰክሩለት ስለምትፈልጉ አንድ ግለሰብ ማስታወሻ አዘጋጁ። ከዚያም በመደበኛነት በጸሎታችሁ አስቡት። | ኢየሱስ ክርስቶስን በሕይወታችን ቀዳሚውን ስፍራ እንዳንሰጠው እንቅፋት የሚሆኑብንን ነገሮች ዝርዝር አዘጋጁ።<br>***ቁጥር 5*** “እርሱን ስሙት” ይላል። በዚህ ሳምንት እግዚዘብሔር የሚናገራችሁን ነገር ለመስማት ጊዜ ስጡ። |

| | ሀ4 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – የፍቅር ተምሳሌት | ሀ4 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – የትህትና ትምህርቶች |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ዮሐንስ 13: 1-17*<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ዮሐንስ 13: 15*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ኢየሱስ እውነተኛ አገልጋይ ነበር።<br><br>እኛም ሌሎችን ማገልገል አለብን። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ዮሐንስ 13: 1-17*<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** *ዮሐንስ 13: 15*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ኢየሱስ ትሁት አገልጋይና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ታዛዥ ነበር።<br>በክርስትና አገልግሎት ትህትና ዋነኛና ማዕከላዊ ነገር እንደሆነ እንማራለን። |
| መግቢያ | ኢየሱስ ክርስቶስ ይኖርበት የነበረው አገር ደረቅና ሞቃታማ ነበር። (ይህን ተማሪዎቹ ከሚኖሩባቸው አካባቢዎች ጋር አወዳድሩት።) በዚያ አካባቢ ለነበሩ ሰዎች በአቧራማ ጎዳናዎች መጓዝ የተለመደ ነበር። ስለዚህም ወደ አንድ ቤት ሲደርሱ የቤቱ ባለቤት እራት ከማቅረቡ በፊት ለእግራቸው ውኃ በማቅረብ እግራቸውን መታጠባቸውን እርግጠኛ መሆን ነበረበት። (ምናልባትም ተማሪዎቻችሁ ባሉበት አካባቢ ባሕል አንድ እንግዳ ወደ አንድ ሰው ቤት ሲገባ የሚደረጉ ነገሮችን ተነጋገሩባቸው።) | ጌታ ኢየሱስ የክርስትና ሕይወት አንዳንድ አስፈላጊ እውነቶችን የሚያስተምረው ምሳሌዎችን በመጠቀም ነበር። በዚህ አጋጣሚም ትምህርቱን በተግባር ለማስተማር የመረጠው "በተግባራዊ ምሳሌዎች" ነበር። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>ይህ የሆነው ኢየሱስ ከመሰቀሉ ከአንድ ቀን በፊት ነበር። ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የመጨረሻውን እራት እየበላ ነበር። ከደቀ መዛሙርቱ አንዳቸውም በማህበረሰቡ ልማድ እግራቸውን መታጠብ እንዳለባቸው አላስታወሱም ወይንም ደግሞ ለአስፈላጊነቱ ትኩረት አልሰጡትም። ኢየሱስ ያን ለማድረግ ተዘጋጀ። ***(ቁጥር 4 -5)***<br><br>ጴጥሮስ ኢየሱስ እግሩን እንዲያጥበው ፈቃደኛ አለመሆኑን ተናገረ።<br><br>ኢየሱስም ይህን ማድረግ እንዳለበትና ካላደረገ ግን ከእርሱ ጋር ምንም ድርሻ እንደማይኖረው ገለጸለት። ***(ቁጥር 8)***<br><br>ኢየሱስ ይህን የእግር መታጠብ ጊዜ የተጠቀመበት ሁላችንም በኃጢአት መቆሸሻችንና ከኃጢአታችን መንጻት እንዳለብን እንዲሁም በመስቀል ላይ ስለእኛ ሲል ስለሞተ ይህን ማድረግ የሚችለው እርሱ ብቻ እንደሆነ ለማሳየት ነበር።<br><br>ኢየሱስ ከዚህ በተጨማሪ ሊያሳየን የፈለገው ዝቅ ብለን ሌሎችን ማገልገል እንዳለብን ነው። ዝቅ ብለን አንዳችን የሌላችንን እግር የማጠብ ጠቀሜታ ግለጹላቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካ በዓልን አብሮ እያከበረ ነበር። በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ከግብጽ ሲወጡ የተፈጸሙ ነገሮችን እያስታወሳቸው ነበር።<br><br>በዚህ የእራት ጊዜ ነበር ሁለት ትምህርቶችን በተግባር ያስተማራቸው።<br><br>በመጀመሪያ እርሱ የሎሌን ቦታ ወሰደ። የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ። በዚህም በጣም የተናቁ ስራዎችን ለመስራት ዝግጁ መሆኑን በማሳየት ለእነርሱ ምሳሌ ሆነላቸው። (ቁልፍ ጥቅሱን እዩት።)<br><br>ከዚህ በተጨማሪም ሁላችንም ከኃጢአታችን መንጻት እንዳለብን አሳያቸው። (ለዚህም የመታጠብን ምሳሌ ተጠቅሞ አስረዳቸው። (***ቁጥር 10)*** ነገር ግን ክርስቲያኖች ከሆንን በኋላ በየቀኑ እግራችንን መታጠብ ያስፈልገናል። ምክንያቱም በየቀኑ ኃጢአትን እናደርጋለን። የኃጢአት ይቅርታም ያስፈልገናል።<br><br>ተማሪዎቻችሁ ይህን መረዳት እንዲችሉ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ያለውን ነገር እዩት።<br><br>በሁለተኛ ደረጃ ኢየሱስ ዳቦና ወይን ወስዶ ዳቦው የሚሰቀለው የእርሱ አካል ሲሆን ወይኑ ደግሞ በመስቀል ላይ የሚፈሰው ደሙ እንደሆነ ተናገረ። ***(ሉቃስ 22: 19 እና 20 አንብቡ።)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በሚቀጥለው ሳምንት ክርስቲያኖች አንዳቸው ሌላኛውን እንዴት በተግበራዊ መንገድ ማገልገል እንደሚችሉ ተወያዩበት። በሚቀጥለው ዓመት ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያለ ቡድንን በተግባራዊ መንገድ እንዴት ማገልገል እንደምትችሉ አስቡ። | ዛሬ ትህትናን በሕይወታችን የምንለማመድባቸውን መንገዶችን ተወያዩባቸው። ለእግዚአብሔር በሕይወታችን ቀዳሚ ስፍራ መስጠት የምንችላባቸውን ተግባራዊ መንገዶች አስቡ። በትህትና በማገልገል የሚታወቅ አንድ ክርስቲያን ሕይወትን በተመለከተ ጥናት አካሂዱ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ኢየሱስ በምድር ላይ ሲመላለስ ሰዎችን እንዴት ነበር የሚያገለግለው?<br>ከዚህ በተጨማሪም ኢየሱስ ምንም እንኳን ክርስቲያኖች ብንሆንም ኃጢአት ልናደርግ እንደምንችልና ከእርሱ የኃጢአት ይቅርታ በየቀኑ መቀበልና ከኃጢአት መንጻት እንዳለብን አስተማረን። | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>በዚህ አጋጣሚ ጴጥሮስ ምን ትምህርት የተማረ ይመስላችኋል?<br><br>ከኃጢአት መንጻት ምን ማለት ነው? ከጌታ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲኖረንና በሕይወታችን ፈቃዱን ለመከተል ምን ማድረግ አለብን? |

| | *ሀ4 – ደረጃ 3*<br>*ትምህርት 2 – የጴጥሮስ ሕይወት*<br>*ርዕስ – ጌታውን ካደ።* | *ሀ4 – ደረጃ 4*<br>*ጥናት 2 – የጴጥሮስ ሕይወት*<br>*ርዕስ – የታማኝነት ትምህርት* |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: ***ሉቃስ 22: 31-34, 54-62***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ :** ***ሉቃስ 22: 31-32***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>የኢየሱስ ነኝ ማለት ከባድ ነው።<br>ሁልጊዜም እውነትን መናገር አለብን። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: ***ሉቃስ 22: 31-34, 39-62***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ :** ***ሉቃስ 22: 31-32***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>በራሳችን መተማመንን አስወግደንበኢየሱስ ማም አለብን።<br>ልክ እንጴጥሮስ በኃጢአታችን መጸጸት አለበን። |
| *መግቢያ* | ተማሪዎች ለመዋሸት ዝንባሌ የሚያሳዩባቸውን ወይንም ደግሞ ግማሽ እውነት ብቻ የሚናገሩባቸውን ሁኔታዎች አስቡ። አንዳንዴ እኛም እውነት ለመናገር የምንፈራባቸውን ሁኔታዎች መርምሩ። ጴጥሮስ በእንደዚያ አይነት ሁኔታ ውስጥ ገብቶ እንደነበር ግለጹላቸው። | ጴጥሮስ በፍጹም ኢየሱስን እንደማይክደው እርግጠኛ ሆኖ ተናገረ። እንደውም አስፈላጊ ከሆነ ከእርሱ ጋር ወደ ወህኒ ለመውረድና ለመሞት ዝግጁ መሆኑን ተናገረ። (***ሉቃስ 22: 33***) ትዕቢት ውድቀትን እንደሚቀድም ሁላችንም እናውቃለን። ***(ምሳሌ 16: 18)*** ጴጥሮስን በተመለከተ ከአስፈሪው ውድቀቱ በፊት ትዕቢቱ መቅደሙን እናያለን። |
| *ማጠናቀቅ* | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ጴጥሮስ ኢየሱስን ያሰሩትን ሰዎች እስከ ሊቀ ካህናቱ ቤት ድረስ ተከተላቸው። በሊቀ ካህናቱ ግቢ ውስጥ እስካለው የፍርድ ሸንጎ ድረስ በመሄድ በዚያ ከነበሩ አንዳንድ ሰዎች ጋር ተቀላቀለ።<br>አንዳንዶቹም እርሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ጓደኛ ወይንም ተከታይ እንደሆነ ይጠይቁት ነበር። ሶስት ጊዜም ኢየሱስን እንደማያውቀው በመናገር ካደው፤ ዋሸም።<br>ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ተመለከተ። አውራ ዶሮም ጮኸ። ጴጥሮስም ምን እንዳደረገ አስተዋለ። ወደ ውጭ ወጥቶም ምርር ብሎ አለቀሰ። ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን በጣም በሚፈልግበት ጊዜ አሳዘነው። እንዲሁም ደፋር ሳይሆን ፈሪ መሆኑ ገባው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ። .** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ጴጥሮስ ግራ የተጋባ ይመስላል። ኢየሱስ ስለ ክሕደቱ የተናገረውን ያውቃል። *(22: 34)* ኢየሱስ ክርስቶሰን ለመደገፍ ብርቱ እንደሆነ አሰበ።<br><br>የጭንቁ ጊዜ ሲመጣ ግን እውነቱን ለመናገር ፈራ። በእርግጥም ልክ ኢየሱስ እንደተናገረው ኢየሱስን ሶስት ጊዜ ካደው።<br><br>ኢየሱስን በማሳዘኑ ምን እንደተሰማው አስቡ።<br><br>የጴጥሮስን ፈተና ተፈጥሮ ወይንም ምንነት ተወያዩበት።<br>የት እንደምንሄድ፣ ከማን ጋር እንደምንቀላቀልና እንዴት እንደምናስብ ተወያዩበት።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | የኢየሱስ መሆን ከባድ የሚሆንባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሩ። ከዚያም እነኝህን ምክንያቶች እንድናሸንፍ የሚረዱንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ኪዳኖች ጻፏቸው። ጴጥሮስ ኢየሱስን አሳዝኖታል። ይቅርታን ያገኝ ይሆን? ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር በኃጢአት ከወደቀ በሃላ እንዴት ኃጢአቱን እንደተናዘዘ እዩ። (**2 ሳሙኤል: 11**) በመዝሙር 51 ደግሞ ይቅርታን ተቀበለ። | በጓደኞቻችን ውስጥ ልናያቸው የምንፈልጋቸውን ባሕርያት በዝርዝር እንጻፍ።<br>በዚህ ሳምንት ለኢየሱስ ታማኝ የምትሆኑበትን አንድ ነገር ጥቀሱ።<br>ኢየሱስ ሊሆን ስላለው ነገር ሲያስጠነቅቀው ምን ማለቱ እንደሆነ አስቡ። (**ሉቃስ 22: 32**) |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ለምንድነው አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች የኢየሱስ እንደሆኑ ለመናገር የሚቸገሩት?<br>እውነትን እንዳንናገር የሚከለክለን ምንድነው? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>በእውነት መጸጸታችንን እንዴት ነው መግለጽ የምንችለው?<br>በመደበኛነት ከምን አይነት ጓደኞች ጋር መቀላቀል አለብን? |

| | ሀ4 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – የኢየሱስ መሞት። | ሀ4 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – በሐዘንና በደስታ ውስጥ የሚገኝ ትምህርት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *ማርቆስ 15: 22-40*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ**: *ገላትያ 2: 20*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ኢየሱስ ምንም ኃጢአት አልነበረበትም ፍጹም ነበር።<br>ኢየሱስ በመስቀል ለእኛ ብሎ በመሞቱ ልናመሰግነው ይገባናል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *ሉቃስ 24: 1-12 & 33-49*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** : *ሉቃስ 24: 46-47*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>እኛ እንድን ዘንድ ኢየሱስ ኃጢአታችንን ወሰደልን።<br>ኢየሱስ የኃጢአት ይቅርታና ዘላለማዊ ሕይወት እንድናገኝ ይጋብዘናል። |
| መግቢያ | ጴጥሮስ ኢየሱስን እንዳሳዘነው ተማሪዎችም አንድን ሰው ቢያሳዝኑ ምን ያደርጉ እንደነበር ጠይቋቸው? ጴጥሮስ ለማድረግ የሞከረውንና ያም ደግሞ ምናልባት የማይቻል እንደሆነ አስቡ። | ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በነበረበት ጊዜ ጴጥሮስ ምን እያደረገ እንደነበረ የምናውቀው ነገር የለም። ሆኖም በፋሲካ ማግስት በነበረው ሰንበት ማለዳ ወደ መቃብር እንደሄደ እናውቃለን። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በዚያን ቀን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተገናኘ። *(See ቁጥር 34)* |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>ኢየሱስ ለስቅለት ከከተማ ውጪ እንዴት ተደርጎ እንደተወሰደ አስረዷቸው።<br>እንዴት እንዳደረጉት፣ እንዴት እንደሰደቡትና እንዴት እንዳላገጡበት አስረዷቸው።<br>ሶስቱ የጨለማ ሰዓታት የተአምራት ሰዓታት እንደነበሩና እግዚአብሔር በእነኝህ ሰዓታት እግዚአብሔር በእኛ ኃጢአት ምክንያት የሚቀጣውን የገዛ ራሱን ልጅ ሊያየው እንዳልቻለ እንድንገነዘብ እንደሚረዳን አስረዷቸው።<br>በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በእኛ ምትክ የኃጢአታችንን ቅጣት ወሰደ።<br>ኢየሱስ በሞተበት ሰዓት ምን እንደሆነ ግለጹላቸው። *(ቁጥር 38-39)*<br>በመስቀሉ አጠገብ ቆሞ የነበረውን የመቶ አለቃውን ምላሽ አስረዷቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>በፋሲካ ማለዳ ሴቶቹ እንዴት ወደ መቃብሩ እንደሄዱ አስረዷቸው።<br><br>ምን እንዳጋጠማቸውና የተቀበሉትን መልዕክት ግለጹላቸው።<br><br>ጴጥሮስ ይህን ዜና ሲሰማ ምን እንዳደረገ አስረዷቸው።. (*ቁጥር 12)*<br><br>አንዳንዶቹ ኢየሱስ መነሳቱን ለማመን የተቸገሩት ለምን እንደሆነ ተወያዩበት።<br><br>ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥላቸው ምን እንደሆነ ግለጹላቸው።<br><br>ጴጥሮስና ወዳጆቹ የተነሳውን ኢየሱስን በማየታቸው አስደናቂ ደስታ ውስጣቸው ገባ።<br>ኢየሱስ መከራውን እንዴት ነበር የገለጸው? *(ቁጥር 45-47)*<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | የኢየሱስን በመስቀል ላይ መሞት ጥቅም፣ የቁልፍ ጥቅሱን ትርጉምና ኢየሱስ ለግለሰቦች መሞቱን አስቡ።<br>የኢየሱስን በመስቀል ላይ የመሞት ጥቅም ተወያዩበት። የኢየሱስን መስዋዕትነት ማስታወስ የሚያስችል መስቀል ሰርታችሁ በሚታይ ቦታ ላይ ለመስቀል አስቡ። | ስለ ኃጢአታችን መጸጸታችንን ስለ ምናሳይበት ተግባራዊ መንገድ ተወያዩ።<br>ኢየሱስ ሞትን ስለ ማሸነፉና ስለ ትንሳኤው የሚናገር መዝሙር አዘጋጅታችሁ ዘምሩ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው ለምንድነው?<br>ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለእኛ ብሎ ስለሞተ እንዴት ልናመሰግነው ይገባናል? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ኢየሱስ ሕያው እንደሆነ እንዴት እናውቃለን?<br><br>የዘላለም ሕይወት ማግኘት ማለት ምን ማለት ነው?<br>በእውነት ይቅር እንደተባልን እንዴት እናውቃለን? |

| | ሀ4 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – “ትወደኛለህ??” | ሀ4 – ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – በፍቅር ውስጥ የሚገኝ ትምህርት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *ዮሐንስ 21: 1-17*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ**: *ዮሐንስ 21: 17*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ልክ እንደጴጥሮስ ኢየሱስን ስናሳዝነው ይቅር እንባላለን።<br>ኢየሱስ ልክ እረኛ ለበጎቹ እንክብካቤ እንደሚያደርገው እኛም ሌሎችን እንድናስተምራቸውና እንድንንከባከባቸው ይፈልጋል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *ዮሐንስ 21: 1-20*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ**: *ዮሐንስ 21: 15*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ኢየሱስ አዲስ ጅማሬን ሊሰጠን ዝግጁ ነው።<br>ምንም እንኳን ውድቀታችን ከባድ ቢሆንም ኢየሱስ ለእኛ ያለው ፍቅር አይቀንስም። |
| መግቢያ | ጴጥሮስ ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ሕይወቱን በአዲስ መልክ እንደገና ለመጀመር እየሞከረ ነው። ወደ ተወለደበት አካባቢ ተመለሰ። የቀድሞ ለመጀመር ወደ ገሊላ ባሕር ሄደ። | ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ራሱን በተለያዩ ጊዜያት በመግለጥ ሕያው እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ አረጋገጠላቸው። *(1 ቆሮንቶስ 15: 3-8)* |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>ደቀ መዛሙርቱ ሌሊቱን በሙሉ ሲያጠምዱ አደረ። ነገር ግን ምንም አልያዙም። ወደ ባሕር ዳርቻ እየተመለሱ ነው። ርቧቸዋል፣ ደክሟቸዋል እንዲሁም ተስፋ ቆርጠዋል።<br><br>ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያሉበት ባሕር ዳርቻ ድረስ መጥቶ ጠራቸው። ሆኖም በመካከላቸው እርሱ መሆኑን ለይቶ ያወቀ አልነበረም። አሳ ይኖራቸው እንደሆነ ጠየቃቸው።<br><br>ትዕዛዙን በመቀበል መረባቸውን በጀልባይቱ በሌላኛው ጎን በኩል ጣሉ። እጅግ ብዙ ቁጥር ያለው አሳ አጠመዱ። ይሄኔ ዮሐንስ ኢየሱስ መሆኑን ተረዳ። ምናልባትም ጴጥሮስ ኢየሱስን ለመገናኘት እየዋኘ ወደ እርሱ መጣ።<br><br>ኢየሱስ ሁሉንም ለቁርስ ጋበዛቸው። ጴጥሮስንም በቁርስ ሰዓት ይወደው እንደሆነ ጠየቀው።<br><br>ጴጥሮስም እንደሚወደው ነገረው። ኢየሱስም የእርሱን ተከታዮች (በጎች) እንዲንከባከብለት አዲስ ስራና ኃላፊነት ሰጠው።<br><br>ኢየሱስ ተመሳሳይ ጥያቄ ሶስት ጊዜ ለምን እንደጠየቀው ተወያዩበት።<br><br>ጌታ ኢየሱስ ይህን ትልቅና እጅግ በጣም አስፈላጊ ኃላፊነት ሲሰጠው ምን ያህል ይቅር ቢለው እንደሆነ አስቡ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>ከትንሳኤ በኋላ ኢየሱስ ለተከታዮቹ ከተገለጠባቸው አጋጣሚዎች አንደኛው በገሊላ ባሕር አሳ በማጥመድ ላይ ለነበሩት ለሰባት ደቀ መዛሙርቱ ነበር።<br><br>እጅግ ብዙ አሳዎችን ማጥመድ እንዲችሉ በማድረግ እርሱ መሆኑን አረጋገጠላቸው።<br><br>ደቀ መዛሙርቱ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረው ቁርስ በሉ።<br><br>ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስ በኢየሱስ የመጨረሻ ሰዓታት ለፈጸማቸው ተደጋጋሚ ስህተቶች ከልቡ ንስሐ መግባቱንና መጸጸቱን እርግጠኛ መሆን ፈለገ።<br><br>በሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ፊትም ሶስት ጊዜ ጌታ ኢየሱስን እንደሚወደው ገለጸ።<br><br>አሁን ጴጥሮስ በአዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች እረኛ ሊሆን ነው። ጌታውን ለማገልገል ሁለተኛ እድል ተሰጠው።<br><br>ምንም ብናሳዝነውም እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ምንም በፍጹም እንደማይቀንስና እኛም እንድወደው እንደሚፈለግ ተወያዩበት።<br>እግዚአብሔር እኛ ብንተወው እንኳን እርሱ በፍጹም እንደማይተወን ተማሪዎቻችሁን አስገንዝቧቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በዚህ ሳምንት ኢየሱስን ልትሰሙ የምትችሉበትን ጊዜ ለማመቻቸት ስለሚያስችላችሁ ተግባራዊ መንገድ ተወያዩ።<br>ኢየሱስን በመስማትና ፈቃዱን በመፈጸም ረገድ ስለ ተሳካለት አንድ ታዋቂ ክርስቲያን መረጃ ሰብስስቡ። | የእግዚአብሔር ፍቅርና ይቅርታ እንዴት እንደሚያበረታታን ተወያዩበት።<br>ኢየሱስ አዲስ ጅማሬን ስለሰጠው ታዋቂ ክርስቲያን ሕይወት ጥናት አካሂዱ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ጌታ ስላደረገልን ነገር ሁሉ ፍቅራችን መግለጽ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስቡ። እኛ ከልባችን ከተጸጸትን ጌታን ብናሳዝነውም እንኳን እንደገና እንድናገለግለው ከአንድ ጊዜ በላይ ደጋግሞ እድል ሊሰጠን እንደሚችል ንገሯቸው።. | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር እንዴት ነው የምንረዳው?<br>እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር እንዴት ነው በተግባር የምናረጋግጠው? |

| | ሀ5 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – የጴጥሮስ ስብከት | ሀ5 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – ጰንጤቆስጤ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***የሐዋርያት ሥራ 2: 1-43***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***የሐዋርያት ሥራ 1: 8***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>*መንፈስ ቅዱስ ለኢየሱስ ተከታዮች ስጦታ ነው።*<br>*የደቀ መዛሙርቱ መልእክት እኛ ንስሐ እንድንገባና የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንድንቀበል የሚነግረን መልእክት ነው።* | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***የሐዋርያት ሥራ 2: 1-42***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***የሐዋርያት ሥራ 2: 38***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ጰንጤቆስጤ የአይሁድ ክብረ በዓል ሲሆን ፋሲካ ካለፈ ከአምስት ቀናት በኋላ ይከበራል። ከጴጥሮስ ስብከት በኋላ ቤተ ክርስቲያን ተወለደች። |
| *መግቢያ* | በሕይወታቸው ትልቅ ለውጥ ቢከሰት ልጆች ምን ሊሰማቸው እንደሚችል እንዲያስቡ ጠይቋቸው። አዲስ ትምህርት ቤት፣ አዲስ ቤት፣ በቤተ ሰብ ውስጥ የሚከሰቱ አዳዲስ የተለወጡ ሁኔታዎች። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ስላረገ ደቀ መዛሙርቱ እርሱ የጀመረውን ስራ የመቀጠል ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። ይህም በእነርሱ ሕይወት ትልቅ ለውጥ ነው። | የልደት ቀን፣ ሌሎች ክብረ በዓላትና ኃይማኖታዊ በዓላት በሁሉም ቤተ ሰቦች ዘንድ ትልቅ ስፍራ እንዳላቸው እንዲያስቡ አድርጓቸው። በተከታዮቹ ወራት ስላሉ ልዩ ቀናት አስቡ። አይሁዳውያን የጰንጤ ቆስጤ ቀንን የፋሲካ በዓልን ካከበሩ ከአምስት ቀናት በኋላ ያከብሩ ነበረ። የፋሲካ በዓል አይሁዳውያን ከግብጽ ከወጡ ከ50 ቀናት በኋላ ማክበር የጀመሩት በአል ነበር። ይህም ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ሕግን ሲቀበል ማክበር የጀመሩት በዓል ነበር። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ቃል የገባላቸውን የመንፈስ ቅዱስ መምጣትን/መውረድን ይጠባበቁ ነበር። ***(የሐዋርያት ሥራ 1: 8)***<br><br>በጰንጤቆስጤ ቀን ልክ በቁጠር 2 እና 3 እንደተገለጸው መንፈስ ቅዱስ መጣ።<br><br>ደቀ መዛሙርቱ ከሌሎች አገሮች ይህን በዓል ለማክበር የመጡ ሰዎች ሁሉ በሚረዷቸው ሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ።<br><br>አንዳንዶች ደቀ መዛሙርቱ መጠጥ ጠጥተዋል አሉ። ጴጥሮስ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ለተሰበሰበው ሕዝብ ምን እንደሆነ አስረዳቸው። እግዚአብሔር በትንቢተ ኢዩኤል ውስጥ በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት መንፈስ ቅዱስ መምጣቱን ነገራቸው። ***(ኢዩኤል 2: 28-32)***<br><br>በድፍረትም ለኢየሱስ መሞት ኃላፊነቱን መውሰድ ያለባቸው እነርሱ እንደሆኑ ነገራቸው። እግዚአብሔር ግን ኢየሱስን ከሙታን እንዳስነሳው ጨምሮ ነገራቸው።<br><br>ይህን የሰሙት ሰዎችም ፍርሃት ሞላባቸው። ምን ማደረግ እንዳለባቸው ጠየቁት። ጴጥሮስም ንስሓ እንዲገቡና እንዲጠመቁ ነገራቸው። በዚያን ቀን ሶስት ሺህ ሰዎች አመኑ። የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮችም ሆኑ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የገባላቸው ተስፋ ማለትም የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በሚያስደንቅ ሁኔታ በጰንጤቆስጤ ቀን ተፈጸመ።<br>መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ምን እንደሆነ ግለጹላቸው።<br>ጴጥሮስ አይሁዳውያን ለኢየሱስ መሞት ኃላፊዎች መሆናቸውን ነገራቸው። በመጨመረም ይህን እነርሱ የገደሉትን ኢየሱስን ከሙታን እንዳስነሳው፣ በሰማይም ከፍ ከፍ እንዳደረገው ጨምሮ ነገራቸው። አያይዞም ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ካለ በኋላ መንፈስ ቅዱስን እንደላከላቸው ገለጸላቸው። በዚያን ቀን ያመኑት የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ አባላት ሆኑ። ቤተ ክርስቲያን በዚያን ቀን ጀመረች እስከዛሬም ድረስ አለች።<br>ባመኑት ሰዎች ሕይወት ምን እንደሆነ ተወያዩበት። ***(ቁጥር 38-39ን እዩ። )***<br>ሕይወታቸው እንደተለወጠ ለማሳየት ምን እንዳደረጉ አስተውሉ። ***(ቁጥር 42)***<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | *መንፈስ ቅዱስ ለመመስከር እንዴት ኃይል እንደሚሰጠን አስቡ።*<br>በዓለም ሁሉ መልካሙን ዜና የማሰራጨት አሰፈላጊነትን ተወያዩበት።<br>በዚህ ሳምንት ተማሪዎች መመስከር እንዴት እንደሚችሉ በቡድን ውይይት ያድርጉ።<br>ከብዙ አመታት በፊት የነበረውን የንስሐ አይነት ለማወቅ ሞክሩ። | የመንፈስ ቅዱስ ስራን አስፈላጊነት ተወያዩበት።<br>እንደቤተ ክርስቲያን በመቀራረብ አብሮ አንድ መሆን ያለውን ጥቅም ተወያዩበት።<br>በፈጣን እድገት ያለች አንድ ቤተ ክርስቲያን ጥቀሱ። የዚህችን ቤተ ክርስቲያና ባሕርያትን ዘርዝሩ። |
| ከሕይወት ጋር ማዛመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ምስክር መሆን ማለት ምን ማለት ነው?<br>ንስሐ መግባት ምን ማለት ነው? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ጰንጤቆስጤ በዚህ ዘመን ላለችው ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?<br><br>በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞች መካፈልና በቤተ ክርስቲያን ሕብረት ውስጥ አካል የመሆን ልዩነትን ተወያዩበት። |

| | ሀ5 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – ጴጥሮስ ሲፈውስ | ሀ5 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – ጴጥሮስ ሽባውን ሰው ፈወሰው። |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: የሐዋርያት ሥራ 3: 1-16**<br>**ቁልፍ ጥቅስ: የሐዋርያት ሥራ 3: 6**<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ኢየሱስ ክርስቶስ በሽታንና ሕመምን የመፈወስ ኃይል አለው።<br>ብንታመንበት ሕይወታችንን ለመለወጥ ስልጣን አለው። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: የሐዋርያት ሥራ 3: 1-26**<br>**ቁልፍ ጥቅስ: የሐዋርያት ሥራ 4: 10**<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>እግዚአብሔር እኛን በትክክለኛው ጊዜና በትክክለኛው ቦታ ያስቀምጠናል።<br>ሽባውን ሰው የፈወሰው የእግዚአብሔር ኃይል እንጂ የደቀ መዛሙርቱ ኃይል አልነበረም። |
| መግቢያ | ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ስለደጉ ሳምራዊና "ጎረቤታቸውን ስለ መውደድ" የነገራቸውን ምሳሌ አልረሱትም። (**ሉቃስ 10: 25-37**) ልክ ይህን ሰው ሲያዩት ኢየሱስ እንዳደረገው ማድረግ እንዳለባቸው ተረዱ። | የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ዋነኛ አስተምህሮት ለሌሎች ስለ መጠንቀቅና እንክብካቤ ስለ ማድረግ ነበር። ያለማቋረጥ ደቀ መዛሙርቱ ለሌሎች ሰዎች ያለውን ፍቅር እንዲያዩ አድርጓል። በተለይም ደግሞ የተቸገሩ ሰዎች አፍቃሪ እንደነበረ በሚገባ አሳይቷቸዋል። ሌላው የነገራቸው ነገር ደግሞ እርሱ ከሄደ በኋላ እርሱ ካደረገው ይልቅ ትልልቅ ነገሮችን እንደሚያደርጉ ነበር። (**ዮሐንስ 14: 12**) |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ጴጥሮስና ዮሐንስ ለመጸለይ ወደ መቅደስ እየሄዱ ነበር።<br><br>ከልጅነቱ ጀምሮ ለአርባ አመታት መራመድ የማይችል ሰው ተገናኛቸው።<br><br>ፍራንክ እንዲሰጡት ለመናቸው። ነገር ግን ጴጥሮስ የተሻለ ነገር እንደሚሰጠው ነገረው። ይህም ፈውስ መሆኑን ነገረው። ሰውየው በእግሮቹ እንዲቆም ረዳው። ሰውዬውም እግዚአብሔርን እያመሰገነ መዝለልና ከወዲህ ወዲያ መራመድ ጀመረ።<br><br>ይህ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ተዓምር ነበር።<br><br>ሕዝቡ ሲሰበሰብ ጴጥሮስ ሽባው ሰው የተፈወሰው በእነርሱ ኃይል ሳይሆን እነርሱ በሰቀሉት በኢየሱስ ስም መሆኑን ነገራቸው። (**ቁጥር 16**)<br><br>የሰውዬውን እምነት ጥንካሬ በቁጥር 16 ላይ ተመልከቱ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሁለትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ልክ የጰንጤቆስጤ በአል እንደተጠናቀቀ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለመጸለይ ወደ መቅደስ ሄዱ። አንድ ሽባ ሰው አዩ። ኢየሱስ ቢሆን ምን ሊያደርግ እንደሚችል አስቡ።<br>በእምነት ጴጥሮስ ከተቀመጠበት ሰውዬው እንዲነሳ ረዳው።<br>ወዲያውም ሰውዬው ተፈወሰ። እየተራመደና እየዘለለም ወደ መቅደሱ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሄደ።<br>ሙሉ በሙሉ ተፈወሰ።<br>ልክ ኢየሱስ እንዳደረጋቸው ተአምራት አሁንም የኢየሱስ ኃይል በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በደቀ መዛሙርቱ አልፎ እየሰራ እንዳለ ይህ ማስረጃ ነበር።<br>ጴጥሮስ በስብከቱ እንደገለጸው ኢየሱስ ማን እንደሆነና አሁንም ምን ማድረግ እንደሚችል አስቡ!<br>ለምን እግዚአብሔር የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት በፈውስ ኃይል እንዴት ሊያስታጥቃቸው አስቡ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | የፈውስ ተአምርን አስቡ። ሁሉም ሰዎች ለምን እንደማይፈወሱ ጨምራችሁ አስቡ።<br>ክርስቲያኖች እስከምድር ጫፍ ድረስ ሄደው ከመመስከራቸው በፊት ለምን በቤታቸው (በኢየሩሳሌም) መመስከር እንዳለባቸው ተወያዩበት።<br>አስደናቂ ተአምር በሕይወቱ የተከናወነለት የዚህ ዘመን ክርስቲያንን በተመከተ መረጃ ሰብስቡ።<br>በኢየሱስ ስንታመን በሕይወታችን ሊያደርግ ስለሚችለው ድንቅ ለውጥ ተወያዩ። | ከኢየሱስ ጋር ጊዜን ማሳለፍ እንዴት የቀን ውሏችንና ምስክርነታችንን እንደሚያሳከልን ተወያዩበት።<br>እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላችሁ፣ ሌሎችንም ማገልገል እንድትችሉ እድል እንዲሰጣችሁ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አብራችሁ ጸልዩ።<br>ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስን ከካደ በኋላ እንዲህ በጣም መለወጡ ለምን እንደሆነ አስቡበት። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ለምንድነው እግዚአብሔር ሁሉንም ሰዎች የማይፈውሰው?<br>ዕለት ዕለት በእግዚአብሔር መታመን የምንችለው እንዴት ነው? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>እግዚአብሔር እንድትሆኑ በሚፈልግበት ላይ መሆናችሁን በምን ታውቃለችሁ?<br>እግዚአብሔር ሕይወታችንን ስለ ለወጠና ኃጢአታችንን ይቅር ስላለን እንዴት ነው የምናሰግነው? |

| | ሀ5 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – የጴጥሮስ ምስክርነት | ሀ5 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – በሸንጎው ፊት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** **የሐዋርያት ሥራ** 4: 1-22<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** **የሐዋርያት ሥራ** 4: 12<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>*መንፈስ ቅዱስ በጴጥሮስ ሕይወት ትልቅ ለውጥ አመጣ።*<br>ክርስቲያኖች ለጌታ ሊቆሙ ይገባል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** ***የሐዋርያት ሥራ 4: 1-31***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***የሐዋርያት ሥራ 4: 13***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>እግዚአብሔር ለኃይማኖት መሪዎች መመስከር እንዲችል ጉልበትና ብርታት ሰጠው።<br>አማኞች ምንም ዋጋ ሊያስከፍላቸው ቢችልም ለሌሎች ስለ አየሱስ ክርስቶስ መናገር እንዲችሉ መዘጋጀት አለባቸው። |
| *መግቢያ* | ባለፈው ትምህርት ምን እንደሆነ በክለሳ መልክ ተመልሳችሁ እዩት። በአንዳንድ አገሮች ለኢየሱስ ክርስቶስ ብትቆሙ ልትሰደዱና እንደውም ወህኒ ቤት ውስጥ ሊያኖሯችሁ እንደሚችሉ ተማሪዎቻችሁን አስታውሷቸው። በዚህ በአሁኑ ታሪክ ጴጥሮስና ዮሐንስ በኃይማኖት መሪዎች ስደት ሲደርስባቸው እናያለን። | ጴጥሮስ እንደገና ትልቅ ስብከት ሰበከ። ***(ምዕራፍ 3)*** ያመኑት ሰዎች ቁጥር ወደ አምስት ሺ ሰዎች አካባቢ ይገመታል። ***(ቁጥር 4)*** የኃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን ሲሰቅሉት የእርሱ ጉዳይ ያለቀለት አድርገው አስበው ነበር። እንደውም አሁን ባሰበት! |
| *ማጠናቀቅ* | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>የኃይማኖት መሪዎች የኢየሱስን ስብከት ሰምተው ታወኩ። ምክንያቱም ሕዝቡን ማስተማር የእነርሱ *(የኃይማኖት መሪዎቹ)* ስራ ነበርና። ጴጥሮስ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው እንደሆነ እየሰበከ ስለነበረ ነው።<br><br>ጴጥሮስና ዮሐንስ ተያዙ። በወህኒ ቤትም አኖሯቸው።<br><br>በቀጣዩ ቀን ልክ እንደኢየሱስ የኃይማኖት ባለስልጣናት ባሉበት ፍርድ ሸንጎ ፊት ይቀርቡ ነበር።<br><br>ጴጥሮስ ሽባውን ሰው በምን ኃይል እንዲራመድ እንዳደረገው ጠየቁት።<br><br>ጴጥሮስም በኢየሱስ ስም ውስጥ ያለው ኃይል ይህን ሰው እንዳደነው ነገራቸው። (***ቁጥር 10)***<br><br>የኃይማኖት መሪዎቹ በዮሐንስና በጴጥሮስ ድፍረት እጅግ በጣም ተደነቁ። ስለ ኢየሱስ መስበክ እንዲያቆሙ አዘዟቸው።<br><br>ጴጥሮስም ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን መታዘዝ እንደሚገባቸው ነገራቸው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት 3. ፈጸመ** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ጴጥሮስና ዮሐንስ ታሰሩ። የአሁዳውያን ሸንጎ አስፈላጊነትን ተነጋገሩበት።<br><br>ጴጥሮስ ሽባውን የፈወሰው የኢየሱስ ኃይል እንደሆነ ለተሰበሰበው ሸንጎ አባላት በድፍረት ከነገራቸው በኋላ ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን ነገራቸው። ***(ቁጥር 12)***<br><br>በጴጥሮስና በዮሐንስ ድፍረት ሸንጎው ተደነቁ። የዚህ ምክንያቱም ከኢየሱስ ጋር ስለነበሩ መሆኑን አስተዋሉ።<br><br>በኢየሱስ ስም መስበካቸውን እንዲያቆሙም ነገሯቸው። ጴጥሮስ ግን መልሶ ከሸንጎው ይልቅ መታዘዝ ያለባቸው እግዚአብሔርን እንደሆነ ነገራቸው።<br><br>ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ገዛ ወገኖቻቸው ተመለሱ። በአንድ ላይ ሆነው መልካሙን ዜና በድፍረት መናገር ይችሉ ዘንድ ጸለዩ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br><br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | እንደመሠረት የሚያገለግሉትን ቁልፍ የክርስትና እምነት ነጥቦችን አጠቃሏቸው። የአንድ አማኝ የእምነቱ መሠረት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊሆን እንደሚገባው አስታውሱ። ***(ቁጥር 12)***<br>በእምነታቸው ጽኑ አቋም ስለነበራቸው የታወቁ ክርስቲያኖች ይበልጥ ለማወቅ ሞክሩ። ለምሳሌ ያህል ኤሪክ ሊደል። | በምስክርነታችሁና በእምነታችሁ እንዴት ይበልጥ መጠንከርና በድፍረት መሞላት እንደምትችሉ ተወያዩ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ለሌሎች ስለ ኢየሱስ እንዳንነግራቸው እንቅፋት የሚሆኑብን ነገሮች ምንድናቸው? አንድ አማኝ "ሕያው ድንጋይ" መሆን አለበት ስንል ምን ማለታችን ነው? ***(1 ጴጥሮስ 2: 4 & 5)*** | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ለሌሎች መመስከር እንችል ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንዴት ነው መደገፍ ያለብን?<br>የወንጌል ተቃውሞ እንዴት ነው እምነታችንን የሚያሳድገው? |

| | ሀ5 – ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – ጴጥሮስ ወህኒ ቤት | ሀ5 – ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – የጴጥሮስ ሕይወት<br>ርዕስ – በወህኒ ቤት |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *የሐዋርያት ሥራ 12: 1-19*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ**: *1 ዮሐንስ 5: 14*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ስደት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል።<br>መጽሐፍ ቅዱስ እኛን እንደሚወደንና ለእኛ መልካም የሆነውን እንደሚያውቅ ይነግረናል። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: *የሐዋርያት ሥራ 12: 1-19*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ**: *1 ዮሐንስ 5: 5*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ልክ ጴጥሮስ እንዳደረገው በክፉ ጊዜ እንኳን ሳይቀር በእግዚአብሔር መታመን አለብን።<br>እግዚአብሔር ለሰው የማይቻሉ ነገሮችን ያደርጋል። እኛ ማድረግ የምንችላቸውን ደግሞ እኛው እንድናደርጋቸው ይተዋቸዋል። |
| *መግቢያ* | ጌታ ኢየሱስ አለም እርሱን እንደጠላችው ሐዋርያትንና ሌሎችን የእርሱ የሆኑትን ሰዎችም እንደምትጠላቸው ተናገረ። (*ዮሐንስ 15: 18*). ገና ጨቅላ ሕጻን ሳለ በንጉስ ሄሮድስ ለጥቂት ሊገደል እንደነበረ እናስታውሳለን። አሁን ደግሞ የሄሮድስ የልጅ ልጅ በጴጥሮስ ላይ ተመሳሳይ ነገር ሊያደርግ እየተዘጋጀ ይገኛል። | አሁንም ጴጥሮስ ስለእምነቱና ስለ ሰብከቱ ታስሯል።ለምርመራ እንደነገ ሊቀርብ ዛሬ በወህኒ ቤት ውስጥ ከባድ እንቅልፍ የወደቀበት እምነቱ ትልቅ ስለነበረ እንደሆነ ግልጽ ነው። ጴጥሮስ በኋላ በመልዕክቱ የጻፈውን እውነት አሁን ተረድቶት ይሆን? *(1 ጴጥሮስ 5: 7)* |
| *ማጠናቀቅ* | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>ንጉስ ሔሮድስ ያዕቆብን አስገደለው። ይህም አይሁዳውያንን ደስ እንዳሰኛቸው ስላወቀ ጴጥሮስን ደግሞ ወህኒ ቤት ውስጥ እንዲታሰረ አደረገው።<br>ጴጥሮስ አሁን በወህኒ ቤት ውስጥ ሆነ በሕዝብ ፊት ቀርቦ በይፋ የሚመረመርበትን ጊዜ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።<br>ቤተ ክርስቲያንም ለመጸለይ ተሰብስባለች።<br>ለምርመራ ከሚቀርብበት ቀን በፊት ባለው ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ከወህኒ ቤት እንዲያመልጥ አደረገው።<br>ከእስር ቤት ካመለጠ በኋላ ወዳጆቹ ወደ ሚጸልዩበት ቤት ሄደ።<br>በሩን የከፈተችው አገልጋይ ሴት ጴጥሮስ በደጅ መቆሙን ነገረቻቸው። ያመናት ግን አልነበረም።<br>ጴጥሮስ በእርግጥም መፈታቱን ሲያውቁ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደመለሰላቸው ገባቸው።<br>በቅዱሳን መካከል ያለን የእውነተኛ ሕብረትጥቅም አስቡ።<br>በመደበኛነት መጸለይ እንደሚገባን አስቡ። በዚህም እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚመልስልን እርግጠኛ መሆንንና እኛም እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን ፈቃድ መቀበልን ይጨምራል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>የጴጥሮስ በወህኒ ቤት መሆን ቤተ ክርስቲያንን እጅግ በጣም አሳስቧታል። ስለዚህም ለእርሱ በብርቱ እየተጸለየ ይገኛል።<br><br>ጴጥሮስ እየተጠበቀ ያለው በአስራ ስድስት ወታደሮች ሲሆን ከሁለቱ ጋር ደግሞ በሰንሰለት እጅ ለእጅ ታስሯል።<br><br>መልአክ ተገለጠ። ጴጥሮስን ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው። ሰንሰለቱን ፈታለት። ከወህኒ ቤቱም እየመራ አወጣው። በተአምር ጴጥሮስ ነጻ ወጣ።<br><br>ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስ ነጻ እንዳወጣው ተረዳ።<br><br>ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ላይ እንዳለች ያውቃል። ሆኖም ግን እንዲህ ያለ ከባድ ነገር እግዚአብሔር ያደርጋል ብላ አምና እንዳልሆነ ደግሞ ያውቃል።<br><br>እግዚአብሔር ለጴጥሮስ ተጨማሪ ስራ እንዳለው ግልጽ ነው። ይህ የሚሞትበት ጊዜ አይደለም። ስለዚህ እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ ውሳኔውን ገለበጠ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br><br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ክርስቲያኖች በመደበኛነት/ሳያቋርጡ የማይጸልዩት ለምንድነው? ተወያዩበት።<br><br>በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ያልነበራችሁበትን ጊዜ አስታውሳችሁ ተወያዩበት።<br><br>ከእግዚአብሔር ምሪት ጋር የተገናኙ ሁሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ፈልጋችሁ ከቡድናችሁ ጋር ተገሯቸው። እንዲሁም ተወያዩባቸው። | በአስቸጋሪ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አስፈላጊ እንደሆነ አስቡ።<br><br>እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚመልስን እያሰብን እንዲሁም በእርሱ ታምነን እንዴት መጸለይ እንዳለብን እናሰብ።<br><br>የቅርብ ጓደኛችሁን ወይንም ደግሞ ዘመዳችሁን እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንዴት እንደመለሰላቸው ጠይቃችሁ የተረዳችሁትን ለሌሎች ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ለምንድነው አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር መንገዶች ምስጢር የሚሆኑብን? (አንደንዶች ይፈወሳሉ፤ ሌሎች ደግሞ አይፈወሱም።)<br><br>እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን ፈቃዱን የምንረዳው እንዴት ነው? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ለምንድነው ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በጸሎት የጠየቅነውን ልክ እኛ በፈለግነው መልክ እንደሚመልስ የምንጠራጠረው?<br><br>የእግዚአብሔር ኃይል ከእኛ ኃይል እንደሚበልጥ የምናውቀው እንዴት ነው? |

| | ሀ6– ደረጃ 3<br>ትምህርት 1 – የአብርሃም ጉዞዎች<br>ርዕስ - በእግዚአብሔር መታመን | ሀ6 – ደረጃ 4<br>ጥናት 1– የአብርሃም ጉዞዎች<br>ርዕስ – የአብርሃም ጥሪ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: ***ዘፍጥረት 12: 1-9***<br>**ቁልፍ ጥቅስ**: ***ዕብራውያን 11: 8***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>አብራም የእምነት ሰው ነበር። እግዚአብሔር የት እንደሚወስደው ባያውቅም እንኳን በእግዚአብሔር ታመነ።<br>ልክ እንደ አብራም እግዚአብሔር እኛን ሲጠራን እኛም ልንታመንበት፣ ልንታዘዘውና ልንከተለው ይገባናል። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ዘፍጥረት 11: 27-32; ዘፍጥረት 12: 1-9***<br>ቁልፍ ጥቅስ : ***የሐዋርያት ሥራ 7: 2-4***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>አብራም የእምነት ሰው ነበር። እግዚአብሔር የት እንደሚወስደው ባያውቅም እንኳን በእግዚአብሔር ታመነ።<br>ልክ እንደአብራም እግዚአብሔር እኛን ሲጠራን እኛም ልንታመንበት፣ ልንታዘዘውና ልንከተለው ይገባናል። በእርግጥም ሕይወታችንን ለእርሱ ልናስረክብ ይገባናል። |
| መግቢያ | አዲስ ት/ቤት ገብተው ያውቁ እንደሆነ ተማሪዎቹን ጠይቋቸው። በዚህ ሂደት ውስጥ የገጠሟቸው ተግዳሮቶች ምን ነበሩ? (አዳዲስ አሰራሮች ጋር መለማመድ፣ አዲስ የጉዞ መስመር፣ አዳዲስ ጓደኞችና አዳዲስ መምህራን በሚሉና በሌሎች ሀሳቦች ዙሪያ ተወያዩ።)<br>ከቡድኑ ውስጥ አዲስ ቤት የቀየሩ ካሉ ጠይቋቸው። በዚህስ የገጠማቸው ተግዳሮት ምን ነበር? አብራምና ቤተ ሰቡ የገጠሟቸው ተግዳሮቶች አዲስና ልዩ ቋንቋ፣ የተለየ ምግብ፣ የአየር ጸባይ ለውጥ፣ አዲስ ባሕልና ልማድ፣ እንዲሁም ከሚያውቋቸው ዘመዶቻቸውና ከአገራቸው ርቆ መሄድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። | **የእርምጃ ክርክር**። ቡድኑን ከዚህ በፊት ወደ ማያውቁት አገር ረዥም ጉዞ በማድረግ ላይ እንደሆኑ እንዲያስቡ ንገሯቸው። እቅዳቸውም በዚህ አዲስ አገር ውስጥ ቤት መስራትና መመስረት እንደሆነ ንገሯቸው። ይህ ምን ተግዳሮቶች አሉበት? (አብራምና ቤተ ሰቡ የገጠሟቸው ተግዳሮቶች አዲስና ልዩ ቋንቋ፣ የተለየ ምግብ፣ የአየር ጸባይ ለውጥ፣ አዲስ ባሕልና ልማድ፣ እንዲሁም ከሚያውቋቸው ዘመዶቻቸውና ከአገራቸው ርቆ መሄድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።)<br>የሚከተሉትን ቃላት በአራት በኤ ፎር የወረቀት መጠን ባላቸው የተለያዩ ወረቀቶች ላይ ጻፏቸው። ***<u>እርግጠኛ አይደለሁም።</u>*** ***<u>ተጨንቄአለሁ።</u>*** ***<u>ተገርሜአለሁ።</u>*** ***<u>ታውኬአለሁ።</u>*** ***<u>ፈርቻለሁ።</u>***<br>በክፍሉ በተለያዩ ጥጎች ላይ እነኚህን ወረቀቶች ለጥፏቸው። ተማሪዎቻችሁም በአደረጉት ለውጥ ምክንያት የሚሰማቸውን ትክክለኛ ስሜት ወደ ሚያሳየው ወረቀት አጠገብ ሄደው እንዲቆሙ አድርጓቸው። ከዚያም በምርጫዎቻቸው ላይ እንዲወያዩ አድርጓቸው። ለምን እንዲህ አይነት ስሜት ተሰማቸው? |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>እግዚአብሔር አብራምን ቤተ ሰቡን ይዞ እርሱ ወደ ሚያሳየው ልዩ አገር እንዲሄድ ነገረው። ይህ ለአብራም ቀላል አልነበረም። በአብራም ጊዜ ጉዞ በጣም አስቸጋሪና ረዥም ጊዜ የሚወስድ አዝጋሚ ነበር። ብዙ የሚያደራጃቸው ነገሮች ከመኖራቸውም ባሻገር ከእርሱ ጋር የሚሄዱ ሰዎችም ነበሩ።<br>እግዚአብሔር ለአብራም እርሱንና ዘሩን እንደሚያበዛቸውና ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርጋቸው ልዩ የተስፋ ቃል ሰጠው። በዚህ ታላቅ ሕዝብ በኩልም የምድር አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩ ነገረው።<br>አብራም ሚስቱን ሶራንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን ይዞ ጉዞውን ጀመረ። ያላቸውን ንብረት ሁሉ ይዘው ተጓዙ። አብራም በዚህን ጊዜ እድሜው 75 ዓመት ነበር።<br>ለጥቂት ጊዜ ከተጓዙ በኋላ እግዚአብሔር ሴኬም በሚባል ስፍራ ለአብራም ተገለጠለት። ያን ምድር ለእርሱና ለዘሩ እንደሚሰጠው ነገረው።<br>አብራምም መሰዊያን ሰርቶ እግዚአብሔርን አመለከ። ከዚያም ተነስቶ በቤቴልና በጋይ መካከል ባለ ኮረብታማ አገር አረፈ። ድንኳኑንም በዚያ ተከለ። እንደገና መሰዊያ ሰርቶ እግዚአብሔርን አመለከ። ከዚያ ስፍራ ተነስቶም ወደ አዜብ ምድረ በዳ ተጓዘ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አንድን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>እግዚአብሔር አብራምን ቤተ ሰቡን ይዞ እርሱ ወደ ሚያሳየው ልዩ አገር እንዲሄድ ነገረው። ይህ ለአብራም ቀላል አልነበረም። በአብራም ጊዜ ጉዞ በጣም አስቸጋሪና ረዥም ጊዜ የሚወስድ አዝጋሚ ነበር። ብዙ የሚያደራጃቸው ነገሮች ከመኖራቸውም ባሻገር ከእርሱ ጋር የሚሄዱ ሰዎችም ነበሩ።<br>እግዚአብሔር ለአብራም እርሱንና ዘሩን እንደሚያበዛቸውና ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርጋቸው ልዩ የተስፋ ቃል ሰጠው። በዚህ ታላቅ ሕዝብ በኩልም የምድር አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩ ነገረው።<br>አብራም ሚስቱን ሶራንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን ይዞ ጉዞውን ጀመረ። ያላቸውን ንብረት ሁሉ ይዘው ተጓዙ። አብራም በዚህን ጊዜ እድሜው 75 ዓመት ነበር።<br>ለጥቂት ጊዜ ከተጓዙ በኋላ እግዚአብሔር ሴኬም በሚባል ስፍራ ለአብራም ተገለጠለት። ያን ምድር ለእርሱና ለዘሩ እንደሚሰጠው ነገረው።<br>አብራምም መሰዊያን ሰርቶ እግዚአብሔርን አመለከ። ከዚያም ተነስቶ በቤቴልና በጋይ መካከል ባለ ኮረብታማ አገር አረፈ። ድንኳኑንም በዚያ ተከለ። እንደገና መሰዊያ ሰርቶ እግዚአብሔርን አመለከ። ከዚያ ስፍራ ተነስቶም ወደ አዜብ ምድረ በዳ ተጓዘ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አንድን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | አብራም ከካራን ምድር ተነስቶ ወደ ቤቴል ያደረገውን ጉዞ የሚያሳይ ካርታ አዘጋጁ። በዚህ ታሪክ የተጠቀሱ ቦታዎችንም ምልክት አድርጉባቸው። እግዚአብሔርን ለማምለክ አብራም የሰራቸውን ሁለት መሰዊያዎችና የታላቁን የመምሬ ዛፍን በዚህ ካርታ ውስጥ ማካተታችሁን አትዘንጉ። | አሁን እግዚአብሔር አብራምን ወደ ሌላ አገር እንዲሄድ ጥሪ ሲያቀርብለት የተሰማውን ስሜት የሚያሳዩ ገላጭ ቃላትን የያዘ ዝርዝር ዛሬ በተማርነው ትምህርት ላይ ተመስርታችሁ አዘጋጁ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>ምንም ቀላል ነገር ባይሆንም እግዚአብሔር አብራምን ወደ ሌላ ምድር እንዲጓዝ ሲጠይቀው ታዘዘ። ይህ ስለአብራም ባሕርይ ምን ያሳየናል? በፍጹም ልንረዳቸው በማንችላቸው ሁኔታዎች ውስጥ እንኳን ሳይቀር በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነት በዕለት ተዕለት ባሕርያችን ላይ እንዴት ነው ተጽእኖ የሚያደርገው? | ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>በጥንድ ወይንም ሶስት አባላት ባሉት ቡድን በዚህ ሀሳብ ላይ ውይይት አካሂዱ።<br>አብራም እግዚአብሔርን ታዘዘ። ይህ አብራም ስለ እግዚአብሔር ስላለው አስተሳሰብ ምን ያስተምረናል?<br>በአንዳንድ ሁኔታዎች እግዚአብሔርን መታዘዝ በፈተናዎች የተሞላ መሆኑን አስቡ።<br>የአብራም ታሪክ ምንም እንኳን ብንፈራም፣ ብንጨነቅም፣ እርግጠኛ ባንሆንም ባሕርያችን ምን መመስል እንደሚገባው ነው ያስተማረን? |

| | ሀ6– ደረጃ 3<br>ትምህርት 2 – የአብርሃም ጉዞዎች<br>ርዕስ - ምርጫዎች | ሀ6 – ደረጃ 4<br>ጥናት 2 – የአብርሃም ጉዞዎች<br>ርዕስ – የአብርሃም ምርጫ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ዘፍጥረት 13: 1-18*<br>**ቁልፍ ጥቅስ :** *ምሳሌ 3: 5 & 6*<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>በሕይወታችን ትክክለኛ ውሳኔዎችን መወሰን አስፈላጊ ነው።<br><br>በሕይወታችን ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን እንድንችል እግዚአብሔርን መለመን ይገባናል። ምሪቱን እንዲሰጠን መለመን አለብን። እግዚአብሔርን ማመስገንና ማምለክ እንዳለብንም አንዘንጋ። | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት:** *ዘፍጥረት 13: 1-18; ዘፍጥረት 14: 1-16*<br>ቁልፍ ጥቅስ: *ኢያሱ 24: 15*<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>አብራም የእግዚአብሔርን ምሪትና እርዳታ ፈለገ። እግዚአብሔርንም አመሰገነ።<br>የእግዚአብሔርን ምሪትና እርዳታ እየፈለግን እንዲሁም ሕይወታችንን ስለባረከ እግዚአብሔርን እያመሰገንንና እያከበረን በምናደርገው ነገር ሁሉ አግዚአብሔርን ማስቀደምና ማወቅ ይገባናል። |
| መግቢያ | እኛ ሁላችን በየቀኑ ምርጫዎችንና ውሳኔዎችን እናደርጋለን። ተማሪዎቻችሁ አነስተኛና የእለት ውሳኔዎች ምሳሌዎችን እንዲሰጧችሁ ጠይቋቸው። ከዚያም ሕይወትን የሚለውጡ ትልልቅ ውሳኔዎች ምሳሌዎችን ይንገሯችሁ። እነኝህን ሁለቱን በአንድ ተገላጭ ቻርት ላይ ጎን ለጎን ጻፏቸው። በአንድ ጎን በኩል በቅርብ ጊዜ የወሰኗቸውን ትንንሽ ውሳኔዎች የሚወክል ስዕል ይሳሉ። በሌላኛው ወገን ደግሞ ስለወደፊት ሕይወታቸው ያላቸውን ተስፋ፣ ሕልማቸውንና ጉጉታቸውን የሚወክል ሌላ ስዕል ይሳሉ። በትንንሽ ቡድኖች ሆነውም ስለሳሏቸው ስዕሎች መወያየትና ሀሳብ መጋራት ይችላሉ። ሁላችንም ውሳኔዎችን እንደምንወስንና ምርጫዎችን እንደምናደርግ በዚህ ጊዜም እርዳታና ምሪትን ከሌሎች ማግኘት እንደሚያስፈልገን ግለጹላቸው። ለሁሉም ውሳኔዎቻችንና ምርጫዎቻችን እግዚአብሔር ምሪትን እንዲሰጠን ልንለምነው እንችላለን። | እግዚአብሔርን ማገልገል የምርጫ ጉዳይ ነው።<br>እግዚአብሔርን ለማገልገል በመረጡ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የምናየው ልዩነት ምንድነው?<br>የላይኛውን ጥየቄ መልሶቻችሁን በተገላጭ ቻርት ላይ ጻፉ። በዚህ ትምህርት ስለአብራም አጭር የሕይወት ታሪክ እያጠናን እነኝህን መልሶቻችሁን አትርሷቸው። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>አብራም ከዚህ በፊት ድንኳኑን ወደ ተከበትና በጋይና በቤቴል መካከል ወዳለው ኮረብታማ አገር ተመልሶ መጣ። በዚያ ለእግዚአብሔር መሰዊያን ሰርቶ ነበር። የእግዚአብሔርን ስም እየጠራ ለመጸለይ ሄደ።<br>አብራም ሊወስን የሚገባው ውሳኔ አለው። ከእርሱ ጋር የሚኖሩና በቦታው ምክንያት መጣላት የጀመሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ለሁሉም የሚበቃ ቦታ አልነበረም። ስለዚህ አብራም ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ጋር የሚለያይበት ጊዜ እንደደረሰ አወቀ።<br>አብራም ሎጥ የሚኖርበትን አካባቢ በመጀመሪያ እንዲመርጥ እድል ሰጠው።<br>ሎጥም ለም የሆነውን፣ በቂ ውኃ የሚገኝበትንና በዮርዳኖስ ወንዝ ትይዩ የሚገኘውን ቦታ መርጦ በከተሞቹ አጠገብ ለመኖር ወሰነ።<br>አብራም በከነአን ምድር መኖሩን ቀጠለ።<br>ሎጥ በራሱ ምርጫ የራሱን መንገድ ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር አብራምን ተናገረው። በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅና በምዕራብ በሁሉም አቅጣጫ የሚያየውን ምድር እንደሚያውርሰው ቃል ገባለት።<br>እግዚአብሔር ለአብራም ዘሩን እንደሚያበዛለትና ይህን ምድር ለዘሩ እንደሚያወርስ ቃል ገባለት። አብራም በኬብሮን በሚገኘው በታላቁ የመምሬ አድባር ዛፍ አጠገብ ተረጋግቶ መኖር ጀመረ። በዚያም መሰዊያን ሰርቶ እግዚአብሔርን አመለከ።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት 2. ፈጸመ** | የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።<br>ውይይትና ገለጻ<br>አብራም ውሳኔ መወሰን ነበረበት። ከእርሱ ጋር የሚኖሩና በግጦሽ ቦታ ምክንያት መጣላት የጀመሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ለሁሉም የሚበቃ ቦታ አልነበረም። ስለዚህ አብራም ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ጋር የሚለያይበት ጊዜ እንደደረሰ አወቀ።<br>አብራም ሎጥ የሚኖርበትን አካባቢ በመጀመሪያ እንዲመርጥ እድል ሰጠው።<br>ሎጥም ለም የሆነውን፣ በቂ ውኃ የሚገኝበትንና በዮርዳኖስ ወንዝ ትይዩ የሚገኘውን ቦታ መርጦ በከተሞቹ አጠገብ ለመኖር ወሰነ።<br>አብራም በከነአን ምድር መኖሩን ቀጠለ።<br>ሎጥ በራሱ ምርጫ የራሱን መንገድ ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር አብራምን ተናገረው። በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅና በምዕራብ በሁሉም አቅጣጫ የሚያየውን ምድር እንደሚያውርሰው ቃል ገባለት።<br>እግዚአብሔር ለአብራም ዘሩን እንደሚያበዛለትና ይህን ምድር ለዘሩ እንደሚያወርስ ቃል ገባለት። አብራም በኬብሮን በሚገኘው በታላቁ የመምሬ አድባር ዛፍ አጠገብ ተረጋግቶ መኖር ጀመረ። በዚያም መሰዊያን ሰርቶ እግዚአብሔርን አመለከ።<br>አብራም ይኖር የነበረው ግጭት በበዛቤት ዘመን ነበር። የሰዶም ጠላቶች ሎጥ ይኖርባት የነበረችውን የሰዶምን ከተማ ወረሯት። በዚያ ይኖር የነበረውን ሎጥን ከንብረቱና አብረውት ከሚኖሩ ሰዎች ጋር አብረው ማርከው ወሰዱት።<br>አብራም ይህን ሲሰማ ጠላቶቹን ለመውጋትና አስረኞቹን ነጻ ለማውጣት ሰራዊት ይዞ ሄደ። የሎጥ አጋቾችን ድል አደረጋቸው። ከሰዶም ንጉስ ምንም ክፍያ መቀበል አልፈለገም። ምክንያቱም ለአብርሃም በጠላቶቹ ላይ ድልን የሰጠው እግዚአብሔር ነበርና።<br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሁለትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | በዛሬው ትምህርት ያየነውን ታሪክ ዜና አዘጋጁለት። ይህም በጋዜጣ መልክ ሆኖ በመጀመሪያው ገጽ ላአለበት። ይህ ተግባር በትንንሽ ቡድኖች ወይንም በጥንድ በጥንድ ሊጠናቀቅ ይችላል። ከዚያም ጋዜጦቹ እንዲታዩ ከተደረገ በኋላ ውይይት ይካሄድባቸው። | ቁልፍ ጥቅሱን አንብቡላቸው። ***ኢያሱ 24: 15***. በዚህ ጥናት ከተማራችሁት ተነስታችሁ አብራም የእግዚአብሔር አገልጋይነቱን የገለጸው እንዴት እንደነበር አብራሩ።<br>በዚህ ትምህርት መጀመሪያ ላይ የተዘረዘሩትን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ባሕርያትን ዝርዝር መልሳችሁ አስታውሱት። ልትጨምሩበትና ልትለውጡት የምትፈልጉት ነገር አለን? በዘመናችን እግዚአብሔርን ማገልገል ምን ልዩነትን ይፈጥራል? |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>አብራም በምርጫዎቹና በውሳኔዎቹ ሁሉ እግዚአብሔርን አስቀድሟል። እግዚአብሔርም ባርኮታል። በሕይወታችሁ በጣም አስፈላጊ ውሳኔዎችን ስትወስኑ እግዚአብሔር እንዲመራችሁና አቅጣጫን እንዲያሳያችሁ ጠይቁት። | ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>ለእያንዳንዱ ተማሪ ምንም ያልተጻፈበት ፖስት ካርድ አድሉ። እግዚአብሔርን በታማኝነት የሚያገለግሉበትን አንድ ነገር እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ የግል የጸሎት ርዕሶቻቸውን በሰጣችኋቸው ፖስት ካርድ ላይ መጻፍ ይችላሉ። ይህም እቤት ሲደርሱ ማስታወሻ ይሆናቸዋል። |

| | ሀ6– ደረጃ 3<br>ትምህርት 3 - የአብርሃም ጉዞዎች<br>ርዕስ – የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች | ሀ6 – ደረጃ 4<br>ጥናት 3 – የአብርሃም ጉዞዎች<br>ርዕስ – በራስ መተማመኑ |
|---|---|---|
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: ***ዘፍጥረት* *17: 1-8; ዘፍጥረት 18: 1-15; ዘፍጥረት 21: 1-5***<br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ማቴዎስ 1: 21***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>ምንም እንኳን አብራም ነገሮችን በራሱ ስሌት ማስኬድ ቢጀምርም እግዚአብሔር አልተወውም።<br><br>እግዚአብሔር አብራም የብዙ ሕዝቦች አባት እንደሚሆን የሰጠውን ቃል አሁንም ደግሞ አረጋገጠለት። ይህ በረከት በአብራም ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በታሪክ ውስጥ ላሉ ሕዝቦች በሙሉ የሚሆን በረከት ነው።<br><br>አንዳንዴ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የማይቻል መስሎ ሲታየን ልንጠራጠረው እንችላለን። ነገሮችን በራሳችን መንገድ ለማስኬድ እንሞክራለን። ይህ ትምህርት የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አምነን እንድንቀበልና እስኪፈጸም ድረስ መጠበቅ እንዳለብን ይነግረናል። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ዘፍጥረት 15: 1-7; ዘፍጥረት 17: 1-19; ዘፍጥረት 18: 1-15***<br>ቁልፍ ጥቅስ: ***ዘፍጥረት 18: 14***<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>እግዚአብሔር ወራሽ ልጅ እንዲሚሰጠው ቃል ገብቶለት ነበር። አብራም እግዚአብሔርን አመነ። ሆኖም እርሱም ሆነ ሚስቱ በጣም አርጅተው ነበር። እስከዚህ ጊዜ ድረስም ልጅ አልነበራቸውም። ስለዚህ ነገሮችን በራሳቸው መንገድ ማስኬድ ፈለጉ።<br><br>እግዚአብሔር በአብራምና በሦራ ጉዳይ ተስፋ አልቆረጠም። እግዚአብሔር አብራም የብዙ ሕዝቦች አባት እንደሚሆን የሰጠውን ተስፋ አጸናለት። ይህ በረከት በአብራም ብቻ የሚወሰን ሳይሆን በታሪክ ውስጥ ላሉ ሕዝቦች በሙሉ የሚሆን በረከት ነው።<br><br>አንዳንዴ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የማይቻል መስሎ ሲታየን ልንጠራጠረው እንችላለን። ነገሮችን በራሳችን መንገድ ለማስኬድ እንሞክራለን። ይህ ትምህርት የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አምነን እንድንቀበልና እስኪፈጸም ድረስ መጠበቅ እንዳለብን ይነግረናል። |
| መግቢያ | ቡድኑን ከዚህ በፊት ቃል ኪዳን ገብተው እንደሆነ ጠይቋቸው። ለቡድኑ አባላት ቃል ገብቶ የሚያውቅ ሰው አለ? የእነኝህን ቃል ኪዳኖች ዝርዝር በተገላጭ ቻርት ላይ ጻፏቸው። ለእነኝህ ቃል ኪዳኖች ምክንያቶቹ ምንድናቸው? (በቡድን ተወያዩበት።) ይህ ትምህርት ምንም እንኳን በማይመስል ሁኔታዎች ውስጥ ቢሆንም እግዚአብሔር የገባውን የተስፋ ቃል ይጠብቃል። | በጥቁር ሰሌዳ ወይንም ደግሞ በተገላጭ ቻርት ላይ ሰዎች በዚህ ዘመን የሚገቧቸውን ቃል ኪዳኖች ዘርዘራችሁ ጻፉ። (የጋብቻ ኪዳኖች፣ ወታደራዊ ቃለ መሓላ፣ ሕጋዊ ስምምነቶች፣ የክፍያ ስምምነቶች ወዘተ...) እንዲህ አይነት ኪዳኖች እስከምን ደረጃ ድረስ እንደሚጸኑ ወይንም ደግሞ እንደሚሰበሩ ተወያዩበት። የዛሬው ትምህርት እግዚአብሔር ኪዳኑን እንደሚጠብቅ ያስተምረናል። |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>እግዚአብሔር አብራም ብዙ ልጆች እንደሚኖሩት ቃል ገብቶለት ነበር።<br>አብራምና ሚስቱ ሶራ ከማርጀታቸውም የተነሳ ነገሮችን በራሳቸው መንገድ ለማስኬድ እየሞከሩ ነበር። እግዚአብሔር ግን በዚህ ምክንያት ኪዳኑን አልሰበረም። እንደውም ከአብራምና ከሦራ ጋር ያለውን ኪዳን አጸናው እንጂ! ለዚህም ምልክት ይሆናቸው ዘንድ አዲስ ስምን ሰጣቸው። አዲሱ ስማቸውም አብርሃምና ሳራ ይባል ነበር።<br>እግዚአብሔር አብርሃም የብዙ ሕዝቦች አባት እንደሚሆን ነገረው። እንዲሁም እግዚአብሔር እርሱ አምላካቸው እንደሚሆንና ምድሪቱን ለእርሱና ለዘሩ እንደሚሰጥ ኪዳን ገባለት።<br>ሶስት ሰዎች ሊጎበኙት መጡ። አብርሃም ለእነርሱ ደግነትን አሳያቸው።<br>ሳራ በሚቀጥለው አመት በዚህን ጊዜ ልጅ እንደምትወልድ እግዚአብሔር ለአብርሃም ነገረው። ይህን ስትሰማ ሳራ ሳቀች። ምክንያቱም አብርሃምም ሆነ እርሷ ልጅ ለመውለድ እጅግ በጣም አርጅተው ነበርና ነው።<br>እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን አጸና። ሳራም ወንድ ልጅ ወለደች። አብርሃምም ልጁን ይስሐቅ ብሎ ጠራው። የይስሐቅ የስሙ ትርጉም “ሳቅ” ማለት ነው። ይህም እግዚአብሔር የማይታመነውን ኪዳኑን ስለፈጸመላቸውና በስተርጅናቸው ትልቅ ደስታን ስላመጣላቸው ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት ሶስትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br>እግዚአብሔር አብራም ብዙ ልጆች እንደሚኖሩት ቃል ገብቶለት ነበር።<br>አብራምና ሚስቱ ሶራ ከማርጀታቸውም የተነሳ ነገሮችን በራሳቸው መንገድ ለማስኬድ እየሞከሩ ነበር። እግዚአብሔር ግን በዚህ ምክንያት ኪዳኑን አልሰበረም። እንደውም ከአብራምና ከሦራ ጋር ያለውን ኪዳን አጸናው እንጂ! ለዚህም ምልክት ይሆናቸው ዘንድ አዲስ ስምን ሰጣቸው። አዲሱ ስማቸውም አብርሃምና ሳራ ይባል ነበር።<br>እግዚአብሔር አብርሃም የብዙ ሕዝቦች አባት እንደሚሆን ነገረው። እንዲሁም እግዚአብሔር እርሱ አምላካቸው እንደሚሆንና ምድሪቱን ለእርሱና ለዘሩ እንደሚሰጥ ኪዳን ገባለት።<br>ሶስት ሰዎች ሊጎበኙት መጡ። አብርሃም ለእነርሱ ደግነትን አሳያቸው።<br>ሳራ በሚቀጥለው አመት በዚህን ጊዜ ልጅ እንደምትወልድ እግዚአብሔር ለአብርሃም ነገረው። ይህን ስትሰማ ሳራ ሳቀች። ምክንያቱም አብርሃምም ሆነ እርሷ ልጅ ለመውለድ እጅግ በጣም አርጅተው ነበርና ነው።<br>እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን አጸና። ሳራም ወንድ ልጅ ወለደች። አብርሃምም ልጁን ይስሐቅ ብሎ ጠራው። የይስሐቅ የስሙ ትርጉም “ሳቅ” ማለት ነው። ይህም እግዚአብሔር የማይታመነውን ኪዳኑን ስለ ፈጸመላቸውና በስተርጅናቸው ትልቅ ደስታን ስላመጣላቸው ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት ሶስትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | ቁልፍ ጥቅሱን አንብቡ። በዚህ ቁልፍ ጥቅስ ውስጥ ያለውን ጥያቄ ለመጽሐፍ ገጸ ማውጫ እንዲሆን አድርጋችሁ ተጠቀሙበት። ይህን ጥያቄ በምታዩበት ወቅት ሁሉ እግዚአብሔር ኪዳኑን እንደሚጠብቅ አስታውሱ። ይህም ኪዳኑ ሊፈጸም የማይችል ሲመስለንም ጭምር መሆኑን አትርሱ። | **በአነስተኛ ቡድኖች**<br>በዚህ ትምህርት ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ አብርሃምና ስለ ሳራ ባሕርይ ምን እንማራለን? ተማሪዎች ሀሳቦቻቸውን በወረቀት ላይ መጻፍ አለባቸው። ከዚያም በቡድን ሆነው ውይይት ያካሂዱ። |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>በእግዚአብሔር ትታመናላችሁ? በቃሉ ውስጥ ባሉት ኪዳኖቹ ታምናላችሁ? ይህ ትምህርት እንዴት ነው በእግዚአብሔር ላይ ያላችሁን እምነት የሚያጠናክረው? | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>በሕይወታችሁ ያሉና ለእግዚአብሔር ከባድ የሚመስሉ ነገሮች አሉ? በሁሉም የሕይወታችሁ ክፍሎች በእግዚአብሔር መታመን እንድትችሉ ይህ ትምህርት ምን አስተዋጸኦ አደረገ? |

| | | |
|---|---|---|
| | ሀ6– ደረጃ 3<br>ትምህርት 4 – የአብርሃም ጉዞዎች<br>ርዕስ – የፍቅር ፈተና | ሀ6 – ደረጃ 4<br>ጥናት 4 – የአብርሃም ጉዞዎች<br>ርዕስ – ተግዳሮቱ |
| | **የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት**: ***ዘፍጥረት 22: 1-14***<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** ***ዮሐንስ 1: 29***<br><br>**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው። አብርሃም አንድያ ልጁን እንዲሰዋ ጠየቀው። አብርሃም እግዚአብሔርን ታዘዘው። ሙሉ በሙሉ ታመነበት።<br>እግዚአብሔር ትልቅ ለጋስ ነው። ይስሐቅን የሚተካ መስዋዕት አዘጋጀ። እግዚአብሔር የእኛን ቦታ ይወስድና ስለ ኃጢአታችን መስዋዕት ሆኖ ይሞት ዘንድ ልጁን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሰጠን። | የመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት: ***ዘፍጥረት 22: 1-19***<br><br>ቁልፍ ጥቅስ : ***ዕብራውያን 11: 17-19***<br><br>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<br>እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው። አብርሃም አንድያ ልጁን እንዲሰዋ ጠየቀው። አብርሃም እግዚአብሔርን ታዘዘው። ሙሉ በሙሉ ታመነበት።<br>እግዚአብሔር ትልቅ ለጋስ ነው። ይስሐቅን የሚተካ መስዋዕት አዘጋጀ። እግዚአብሔር አብርሃም እንደታዘዘውና ያለውን ሁሉ ሊሰጠው እንደተዘጋጀ አወቀ። ስለዚህም እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ኪዳን እንደገና አጸናለት። እግዚአብሔር የእኛን ቦታ ወስዶ መስዋዕት ሆኖ ኃጢአታችንን ይወስድ ዘንድ ልጁን ኢየሱስን ሰጠን። |
| መግቢያ | አንዳንድ ጊዜ የሰዎችን ሁኔታ ለመረዳትና ለመወሰን አንዳንድ ፈተናዎችን እንሰጣቸዋለን። እነኝህ ሰዎች የሚወስዷቸውን ፈተናዎች አይነት በዝርዝር አዘጋጁ። (የመንጃ ፈቃድ፣ የት/ቤት ፈተናዎች፣ የሙዚቃ ትምህርት ፈተና፣ የአይንና የጆሮ ፈተና ወዘተ...) እነኝህ ፈተናዎች ስለሰዎች እውቀት፣ መረዳት፣ አካላዊ ብቃትና ባሕርይ አንድ ነገር ይናገራሉ። በዚህ ታሪክ እግዚአብሔር አብርሃም በእርሱ ያለው እምነት ጠንካራ መሆኑን ለማወቅ እንደፈተነው እናያለን። | ያለእርሱ ልትኖሩ የማትችሉበት አንድ ነገር ወይንም አንድ ሰው አለ? ለአብርሃም እንዲህ አይነቱ ሰው ልጁ ይስሐቅ ነበር። አብርሃም ይስሐቅን ለማግኘት ለረዥም አመታት ጠብቋል። አብርሃም ይስሐቅን ቢያጣ ምን ይሰማዋል ትላላችሁ? |
| ማጠናቀቅ | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>እግዚአብሔር አብርሃምን ልጁን ይስሐቅን እንዲሰዋለት ጠየቀው።<br>አብርሃም የእግዚአብሔርን መመሪያዎቸ ታዘዘ። አብርሃም ለሶስት ቀናት ተጉዞ እግዚአብሔር የጠየቀውን ነገር ለማድረግ እርሱ ወዳሳየው ቦታ ደረሰ።<br>ይስሐቅ አብርሃምን መስዋእቱ የታለ ብሎ ሲጠይቀው እግዚአብሔር መስዋዕቱን እንደሚያዘጋጅ ነገረው። ይህ የሚያሳየው አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ ትልቅ እምነት እንደነበረው ነው።<br>አብርሃም ለእግዚአብሔር ፍጹም ታዛዥ ነበር። ያለውን ነገር በሙሉ ለእግዚአብሔር ለመስጠትና ውድ ልጁን ለመሰዋት ዝግጁ ነበር።<br>እግዚአብሔር አብርሃምን ተጣርቶ ልጁን ይስሐቅን እንዳይጎዳው ነገረው። በእርግጥም እግዚአብሔር የይስሐቅን ቦታ የሚወስድ መስዋዕት አቀረበ። ይህም በግ ነበር።<br>እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሩ ሊቆጥር እስከማይችል ድረስ እንደሚያበዛለት የገባለትን ቃል ኪዳን አጸናለት። እንዲሁም የምድር ሕዝቦች ሁሉ በዘሩ እንደሚባርክ ቃል ገባለት።<br>እግዚአብሔር አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በእኛ ምትክ "የእግዚአብሔር በግ" እንዲሆን ላከው። ካመንንበት በጌታ በኢየሱስ በኩል እግዚአብሔር በደህንነት ይባርከናል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ትምህርት አራትን አጠናቁ።** | **የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አቅርቡት።**<br>**ውይይትና ገለጻ**<br><br>እግዚአብሔር አብርሃምን ልጁን ይስሐቅን እንዲሰዋለት ጠየቀው።<br>አብርሃም የእግዚአብሔርን መመሪያዎቸ ታዘዘ። አብርሃም ለሶስት ቀናት ተጉዞ እግዚአብሔር የጠየቀውን ነገር ለማድረግ እርሱ ወዳሳየው ቦታ ደረሰ።<br>ይስሐቅ አብርሃምን መስዋእቱ የታለ ብሎ ሲጠይቀው እግዚአብሔር መስዋዕቱን እንደሚያዘጋጅ ነገረው። ይህ የሚያሳየው አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ ትልቅ እምነት እንደነበረው ነው።<br>አብርሃም ለእግዚአብሔር ፍጹም ታዛዥ ነበር። ያለውን ነገር በሙሉ ለእግዚአብሔር ለመስጠትና ውድ ልጁን ለመሰዋት ዝግጁ ነበር።<br>እግዚአብሔር አብርሃምን ተጣርቶ ልጁን ይስሐቅን እንዳይጎዳው ነገረው። በእርግጥም እግዚአብሔር የይስሐቅን ቦታ የሚወስድ መስዋዕት አቀረበ። ይህም በግ ነበር።<br>እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሩ ሊቆጥር እስከማይችል ድረስ እንደሚያበዛለት የገባለትን ቃል ኪዳን አጸናለት። እንዲሁም የምድር ሕዝቦች ሁሉ በዘሩ እንደሚባርክ ቃል ገባለት።<br>እግዚአብሔር አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በእኛ ምትክ "የእግዚአብሔር በግ" እንዲሆን ላከው። ካመንንበት በጌታ በኢየሱስ በኩል እግዚአብሔር በደህንነት ይባርከናል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅሱን አብራሩት። ተማሪዎችም እንዲያጠኑት አበረታቷቸው።**<br>**ጥናት አራትን አጠናቁ።** |
| ክለሳ | የዛሬው ቁልፍ ጥቅስ ኢየሱስ የአለምን ኃጢአት የሚያስወግደው ፍጹሙ መስዋዕት የእግዚአብሔር በግ እንደሆነ ያስተምረናል። በእግዚአብሔር አምናችኋል? ጌታ ኢሱስ ክርስቶስን እንደአዳኛችሁ ተቀብላችሁታል? | በዛሬው ጥናታችን ያየናቸው ተግባራት የተከናወኑበትን ቦታ አብርሃም "እግዚአብሔር ያዘጋጃል" የሚል ስያሜ ሰጠው። ጌታ ለእኛ ያዘጋጀልን እንዴት ነው? |
| ከሕይወት ጋር ማዘመድ | **ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?**<br>አብርሃም እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ታመነበት፣ ታዘዘውም። እግዚአብሔርም በዚህ ምክንያት በኃይል ባረከው። የአብርሃምን ምሳሌነት መከተል የምንችለው እንዴት ነው? | ትምህርቱ ሕይወታችንን ምን ያህል ፈትሾታል?<br>አብርሃም ምንም እንኳን እምነቱን ቢፈትነውም በእግዚአብሔር ታመነ፣ ታዘዘውም። የአብርሃምን ምሳሌነት እንዴት ነው መከተል የምንችለው? |

## *ለመምህራን የእርማት መመሪያ*

### ለደረጃ 3 ትምህርቶች

- *ተማሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን ሳያነቡ ትምህርቶቹን ማጠናቀቅ አይችሉም። ስለዚህ አንድ ወይንም ከዚያ በላይ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦችን ማድረግ ይጠበቅባቸው ይሆናል።*
- *ጥያቄዎቹ የተለያዩ ናቸው። እነኝህም cross words እና word grids, እንዲሁም የጎደሉ ቃላትን መሙላት ወዘተ... ናቸው።*
- *ጥያቄዎቹ የተለያዩ አይነቶች የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትሞችን በማንበብ እንዲመለሱ ታስበው የተዘጋጁ ጥያቄዎች ናቸው።*
- *የእኛ አላማ ሁሉም ተማሪዎች የትኛውንም አይነት የመጽሐፍ ቅዱስ እትም ተጠቅመው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ መርዳት ነው።*
- *በየሳምንቱ 20 ነጥቦች ይሰጣቸዋል። በወር ደግሞ ትምህርቶቹ በሙሉ ትክክል ከሆኑ በአጠቃላይ 80 ማርኮች ይሰጣቸዋል።*
- *ደረጃ 3 - ለአንድ መልስ አንድ ማርክ ብቻ ይሰጠዋል።*

### ደረጃ 4 ጥናቶች

- *እነኝህ በደረጃ ሶስት ከሚሰጡት ትምህርቶች በትንሹ ጠጠር ይላሉ።*
- *ተጨማሪ ውስብስብ ጥያቄዎችና መልሶች ያስፈልጋሉ።*
- *በሳምንት ሀያ ነጥቦች በወር ደግሞ 80 ነጥቦች ይሰጣሉ። ይህም ትምህርቶቹ በሙሉ ትክክል ሲሆኑና ጥያቄዎቹ የተሟላ መልስ ሲኖራቸው ነው።*

#### የነጥብ አሰጣጥ ፍንጮች

*መምህራን በመጀመሪያ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ።*

- *እያንዳንዱን ትምህርት መገምገምና መልሶቹ ትክክል መሆን አለመኖናቸውን ምልክት ማድረግ።*
- *በመመሪያው መሰረት ትክክለኛውን ነጥብ መስጠት።*
- *ነጥብ ስንሰጥ የተለያየ አይነት ቀለም ያላቸውን ብዕሮች /እስክርቢቶዎች/ መጠቀም አለበን። ትክክል ለሆኑ መልሶች የ "✓" ምልክት እናድርግ።*
- *ትክክል ላልሆኑ መልሶች ትክክለኛ መልሶቻቸውን አስቀምጡ። የፊደላት ግድፈቶች ካሉም እርማት ስጡ። ለፊደላት ግድፈት ነጥብ አይቀነስም።*
- *በከፊል ትክክል ለሆኑ መልሶች ነጥብ ቀንሱ።*
- *የወሩን ድምር ነጥብ አስቀምጡ። ይህንንም በጀርባ ገፅ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ለይ ጻፉ።*

*አንዳንዴ በአግባቡ ለጋስ መሆን ያስፈልጋል። እንዲሁም ተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን ማጠናቀቅ እንዲችሉ ለማበረታታት ማንኛውንም ነገር ማድረግ አስፈላጊ ነው። በየወሩ መጨረሻ መምህራን አንድ የማበረታቻ ቃል ለተማሪዎች ቢፅፉ መልካም ነው። ይህን ለማድረግም በየትምህርቶቹ ቦታ ተዘጋጅቷል። ጥሩ የቀለም ቅብን፣ ንፅሕናን፣ ተማሪው ያስመዘገበውን ነጥብ፣ ተማሪው ምን ያህል እንደተረዳ የሚገልፁ አስተያየቶችን መጻፍ ይቻላል።*

*አስተያየቶች በተቻለ መጠን የተለያዩ እንዲሆኑ መጣር አለብን። ጥያቄዎች፣ አረፍተ ነገሮች፣ ምልከታዎች፣ ማበረታቻዎች ወዘተ...ይህን ልዩነት ለማሳየት ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ይህ በጥልቅ ማሰብንና የተማሪዎች ፍላጎት መጠበቁን ማረጋገጥ ይጠይቃል። አንድ አረፍተ ነገር ወይንም ደግሞ ጥያቄ በየወሩ የሚደጋገም ከሆነ የሚፈለገውን ግብ ላይመታ ይችላል።*

#### ደረጃ 3

**አጠቃላይ አስተያየቶች**

*"በጣም ጥሩ ስራ! ጥያቄዎቹን በጥንቃቄ እንዳነበብካቸው ያስታውቃል። በተለይም ለመጨረሻው ጥያቄ የሰጠኸው መልስ አስደስቶኛል። ትክክለኛ ቃላትን ተጠቅመሃል።"*

*"ሃይ ዮናታን! ሰለጥረትህ አመሰግንሃለሁ። ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ መሞከርህ ትልቅ ነገር ነው። ያልሰራሃቸውን እኔው አሟልቼልሃለሁ።"*

**መንፈሳዊ አስተያየቶች**

*"ከእስራኤል ልጆች ጋር ሙሴ አስቸጋሪ ጊዜ ነበረው። ሆኖም እግዚአብሔር ሙሴ በራሱ ለነገሮች መፍትሔ እንዲፈለግ ብቻውን አልተወውም።"*

*"ዮሴፍ አባቱ እግዚአብሔርን እንዲወድ ያስተማረውን ትምህርት ፈፅሞ አልረሳውም። ከቤተሰቦቹ በጣም ርቆ በነበረበት ጊዜ እንኳን ይህን ፍፁም አልረሳውም።"*

*"በርጠሎሜዎስ ጌታ ኢየሱስን ለመንካት ቁርጦ ነበር። ማየት ችሏልና ምንም አይቆጨውም። አሁን ለእርሱ ጌታ ኢየሱስ ማለት በጣም ልዩ የሆነ ሰው ነው።"*

#### ደረጃ 4

**አጠቃላይ አስተያየቶች**

*"ሌላ በጣም አስገራሚ ትምህርት! የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮቹን በሚገባ የተረዳሃቸው ይመስላል። እነኝህ ታሪኮች እንዳስደሰቱህም ተስፋ አደርጋለሁ። ትምህርቶችህን በጥንቃቄ ስላጠናሃቸው በጣም አመሰግንሃለሁ። በፍጥነት ልትጨርሳቸው ትችላለህ። ስለዚህ ጥረትህን በሙሉ አደንቃለሁ።"*

*"ራሔል! በጣም ጥሩ ሙከራ! መልሶችሽን አይቻቸዋለሁ። ታሪኩን ሙሉ በሙሉ የተረዳሽው አይመስልም። ምናልባት እንደገና ማንበብ ይጠበቅብሽ ይሆናል።"*

**መንፈሳዊ መልእክቶች**

*"ምሳሌዎች አንዳንድ ጊዜ ሰማያዊ ወይንም ጥልቅ ትርጉም በውስጣቸው የያዙ ምድራዊ ታሪኮች ተብለው ይጠራሉ። በጥናት 3 ያለውን ምሳሌ ጥልቅ ትርጉም ምን እንደሆነ ልታስበው ትችላለህ?"*

*"እስጢፋኖስ በጭካኔ አገዳደል ሞተ። ሆኖም ሞትን አልፈራም። ምክንያቱም አሁንም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በበላይነት እንደሚቆጣጠር ያውቅ ስለነበር ነው። እንዲሁም ቢሞትም እንኳን በሰማይ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንደሚሆን ያውቅ ነበር።"*

bes
bible educational services

© የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት 2007ዓ.ም.

www.besweb.com

በሕግ የተመዘገበ የዩ.ኬ ለጋሽ ድርጅት 1096157